# ፩

## አዲስ ኪዳንን ማብራራት (1)

### ብዙ ጠቃሚ ርእሰ ጉዳዮች ቢኖሩንም ያለን ጊዜ ግን ትንሽ ነው

አዲስ ኪዳንን አብራርተን የምናስተምርበት መንገድ ብሉይ ኪዳንን ከምናብራራበት ዘዴ ጋር በአንዳንድ ሁኔታ ይመሳሰላል፤ ሆኖም በዐጭር ጊዜ ውስጥ ስፊ ሐሳብን አጠቃለን ማቅረብ ያዳግተናል። አዲስ ኪዳንን ከብሉይ ኪዳን ልዩ የሚያደርገው የራሱ የሆነ ባሕርይ አለው፤ ለምሳሌ ለመቶ ዓመታት ወደ ኋላ ተመልሶ የሕዝብን ታሪክ የሚያመላክት ጽሑፍ የለውም፤ የመዝሙራት÷ የጥበባት አባባሎችና የነቢያት መልእክቶች የሉትም። በዚህ ሁኔታ ተደጋግመው የሚያጋጥሙን የጭብጥ ክፍሎች ምዕራፉን በማብራራት ፈንታ መጽሐፉን እንድናብራራ የሚያግዙን ሁኔታዎች የሉም። አብዛኛው የአዲስ ኪዳን ክፍል ቀጥተኛ ትምህርትን የያዘና በቀላሉ ሊያጥሩ በማይችሉ መልእክቶች የተሞላ ነው። ተራኪ ጽሑፎችን የያዙ መጻሕፍት ቢኖሩትም በብሉይ ኪዳን ከሚታዩት ተራኪ መጻሕፍት ባነሰ ትረካና በላቀ ቀጥተኛ ትምህርት ላይ ያዘነብላሉ።

በብሉይ ኪዳን እንደሚታየው አዲስ ኪዳንን ለማብራራት የሚያጋጥመው ዋና ችግር በተለይም ረዘም ባሉት መጻሕፍት ላይ ነው። በመካከለኛ ግምት በአንድ ስብከት ውስጥ ከአንድ ምዕራፍ በላይ መጠቀም የምንችል አይመስልም (ብዙዎቻችን የሚኖረን ግምት ከዚህ ያነሰ ነው)፤ ስለሆነም ከዐሥር ምዕራፎች በላይ የሆነውን መጽሐፍ ለመጨረስ በርከት ያሉ ወራት ያስፈልጉናል። ከዚህም የተነሣ ረጃጅም መጻሕፍትን በተከታታይ ከማስተማር እንቈጠባለን፤ ወይም ከእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ የምንመርጣቸውን ክፍሎች ለማስተማር እንወስናለን። የዚህ ውጤት ዐጫጭር የአዲስ ኪዳን መልእክታትን የምንሰብክ ብንሆንም÷ በረጃጅሞቹ መልእክታት ወይም ወንጌላት ላይ የምንሰብከው እምብዛም ነው።

ስለዚህ ረጅም በሆነ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ላይ እንዴት አድርገን ዝግጅት እንደምናካሄድ ቀጥሎ እንመለከታለን። ለዚህም እንደልምምድ ምሳሌ አድርገን የምንወስደው የዮሐንስን ወንጌል ይሆናል።

በማቴዎስ÷ በማርቆስ ወይም በሉቃስ ወንጌላት ላይ በምንሰብክበት ጊዜ÷ ትረካዊ ወይም በሌሎች ወንጌላት ውስጥ የሚገኙ ተመሳሳይ ሐሳቦችን ስለምናገኝ ሥራችንን በመጠኑም ቢሆን ቀላል ያደርገዋል። የዮሐንስን ወንጌል በምንሰብክበት ጊዜ ግን ይህን ዕድል አናገኝም። በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ከሌሎች ወንጌላት ጋር የሚስማሙ ጥቂት ትረካዎችና ጥቂት ተመሳሳይ ሐሳቦች ይገኛሉ። ችግራችንን የበለጠ የሚያከብደው÷ አብዛኛዎቹ ምዕራፎቹ ረጃጅም የመሆናቸው ጉዳይ ነው። ያም ሆኖ ስብከታችን የግድ በመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎቹ ክፍፍል ላይ ያተኩረ

መሆን የለበትም:: የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፎች አከፋፈል ግን ለመመሪያነት ይረዳናል፤ ምክንያቱም የመጽሐፉ ክፍፍሎች የማያደናግሩ አከፋፈሎች ናቸው::

የዮሐንስን ወንጌል ለመስበክ ብንፈልግና በተከታታይ የምናቀርበውን ስብከት አድማጮቻችን ይሰለቻሉ ብለን ብንፈራ መጽሐፉን በሁለት ክፍል (ከምዕራፍ 1-12፥ ከምዕራፍ 13-21) ልንከፍለው እንችላለን:: በዚህ ሁኔታ ከፋፍለን በምናቀርብበት ጊዜ አንዳንድ የመጽሐፉን ጠቃሚ ጭብጦች እንዘላቸው ይሆናል፤ ሆኖም አድማጩን ከመሰልቸት ለማዳን ይህንን ዋጋ መክፈል አለብን:: የመጀመሪያዎቹን ዐሥራ ሁለት ምዕራፎች የሚያካትቱ ከ12 በላይ ስብከቶችን ማዘጋጀት ብንፈልግ፥ ከዚህ በላይ ልንከፋፍልና የስብከታችንን ብዛት ከቤተ ክርስቲያን ፕሮገራም ጋር በሚስማማ ሁኔታ፥ በየምዕራፉ ልንጨምር እንችላለን::

ምሳሌያዊ ልምምዳችን የዮሐንስን ወንጌል ከምዕራፍ 1-12 በሚመሠረት ዝግጅት ላይ ይሆናል:: በእያንዳንዱ ስብከት ላይ የግድ አንድ ምዕራፍ መካተት የለበትም፤ ለዚህ ልምምድ ሲባል ግን ልንከተለው የሚገባን አዘገጃጀት ይኸው ነው:: ምሳሌያዊ ልምምዳችን በምዕራፍ 7 ላይ የተመሠረተና ረጅም ምዕራፍ ሠላሳ ደቂቃ ለሚሆን ማብራሪያዊ ስብከት እንዴት አድርገን መጠቀም እንደምንችል ለማሳየት የታቀደ ነው፤ (የዐሥራ ሁለት ምራፎች አማካይ ርዝመት ሃምሳ ቍጥሮች ያህል ይሆናል):: ይህን ስናደርግ በተለመዱ ሁለት ወይም ሦስት ጥቅሶች ብቻ አንገደብም፤ የምናቀርበው የስብከት መልእክት የታለመውን ግብ መምታት እንዲችል፥ ምንባቡን ማንበብ፥ ማብራራትና ስለ አተገባበሩም መግለጽ ያስፈልገናል፤ ከዚያም ምንባበቡ ራሱ መልእክት ይሆናል:: መጽሐፍ ቅዱስ ለአድማጮቹ እንዲናገር እንፈልጋለን::

## ማጥናትና ማቀድ

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፥ ይህን ለመሰለው ስብከት ከምንባቡ ጋር በሚገባ መተዋወቅ ዋናው አስፈላጊ ነገር ነው:: ይህን ካላደረግን ሐሳባችንን በተግባር ላይ ማዋል ያዳግተናል:: በተግባር ልምምድ ምሳሌያችን ውስጥ የጥናት ዝግጅታችንን እንደ ፈጸምን እንገምት፤ አሁንም ያዘጋጀነውን መልእክት እንዴት በተግባር ላይ እንደምናውለው መወሰን አለብን:: ምዕራፉ የመገናኛው ድንኳን (ወይም የዳስ በዓል) በሚከበርበት ጊዜ የኢየሱስን መገኘት ያወሳል::

ምዕራፉን ለስብከታችን እንዲያመች አድርገን በተለያዩ መንገዶች በቍጥር ልንከፋፍለው እንችላለን:: ቀላሉ የአከፋፈል መንገድ ምዕራፉን በሦስት ክፍሎች ማለትም የበዓሉ አጀማመር (ከቍጥር 1-13)፥ የበዓሉ አጋማሽ (ከቍጥር 14-36)፥ የበዓሉ ፍጻሜ (ከቍጥር 57-52) በሚል መመደብ ነው:: እነዚህ የአከፋፈል ዘዴዎች የስብከቱን ዋና ዋና ርእሶች አይወክሉ ይሆናል፤ ሥራችንን በተቀላጠፈ መንገድ ለማከናወን ግን ማዕቀፍ ይሆኑናል:: ስብከታችን እየዳበረ በሚሄድበት ጊዜ በማዕቀፉ ምክንያት የት ላይ እንዳለን ማወቅ እንችላለን::

ምናልባት በምዕራፉ ውስጥ ያሉትን ክሥተቶችና የሐሳብ ልውውጦችን አጥንተን ከሆነ ተመራጩ ርእስ «የፈቃደኝነት ችግር» የሚል ይሆናል:: በስብከት ጊዜ የተለያዩ ንዑሳን ርእሶችን ለአድማጮች መስጠት ብንሻ፥ ከዋናው ርእስ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ንዑሳን ርእሶች ለመስጠት እናስብ:: እነዚህ ንዑሳን ርእሶች በምዕራፉ ውስጥ የተዘረዘሩትን የሰዎችን ባሕርይ ማዕከል ያደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ፤ (ለምሳሌ:- ዕብሪተኝነት፥ አድሎአዊነት፥ ግትርነት፥ ንቀት ... ወዘተ) ወይም እነዚህ ነገሮች በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ ያተኩሩ ሊሆኑ ይችላሉ፤ (ለምሳሌ:- በአዲስ ቤተሰብ፥ በተራ ዜጎች፥ በሃይማኖት መሪዎችና በእውነተኛ አማኞች ላይ . . . ወዘተ):: እነዚህ አሠራሮች በአብዛኛው የሰባኪው የአዘገጃጀት ዘዴዎች ናቸው እንጂ የእኛ የአሠራር ልምምድ ጭንቀቶች አይደሉም:: ትኩረት መደረግ ያለበት መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ምንባብ በማብራራት ላይ ነው:: ይህ ምንጊዜም ቢሆን የእኛ ኀላፊነት ነው፤ ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን በራሳችን መንገድና ዘዴ፥ የራሳችንን ስብከት የማዘጋጀትና የማዳበር ነጻነት አለን::

### የበዓሉ መጀመሪያ

ይህን ምዕራፍ ከማስተዋወቃችን በፊት ስለ አይሁድ የመገናኛው ድንኳን ወይንም የዳስ በዓል ምንነት እንገልጻለን:: ይህ በዓል ሰዎች በተለያዩ ዳሶች ውስጥ ሆነው አባቶቻቸው በምድረ በዳ የነበሩበትን ጊዜ በማስታወስ የሚያከብሩትና በዓመት አንድ ጊዜ የሚመጣ ለአንድ ሳምንት የሚዘከር በዓል ነው:: የዓመቱ የመከር መጨረሻም አብሮ ይዘከራል፤ በዓሉ በኢየሱስ ዘመንም እግዚአብሔር ለፍጥረቱ የሕይወት ስጦታ መቻሩን በምስጋና ለመግለጽ በየቀኑ ውሃ የማፍሰስ ሥነ ሥርዓትን ያካትት ነበር::

የዳስ በዓሉን አመጣጥና ዓላማ በተመለከተ የምንገልጸው ይኸው ነው:: የታሪኩን መነሻ ወይንም መግቢያ ስናብራራ ጥንቃቄ ካላደረግን ረጅም ጊዜ በማጥፋት በራሳችን ላይ ችግር እንፈጥራለን:: ድንገት ሰዓታችንን ስንመለከት ቀሪ ሃያ ሦስት ደቂቃዎች ብቻ አሉን ፤ ገና አንድ ጥቅስ በማብራራት አላስተማርንም:: በመጀመሪያዎቹ አምስት ደቂቃዎች ውስጥ ዝግጅታችንን በመቈጣጠር መናገር ካልቻልን በቀሪው ስብከታችን ላይ ችግር እንፈጥራለን::

ሌላው አጭር ማብራሪያችን የኢየሱስን ወንድሞች ይመለከታል:: እነርሱ ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን አላመኑበትም ነበርና፥ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ልዩ የሆኑ ታምራትን በመፈጸም መሲሕነቱን እንዲያረጋግጥ ምጸታዊ በሆነ መንገድ አስተያየታቸውን ሠነዘሩ:: ይህ የተባለበት ጊዜ ጥሩ አጋጣሚ ነበር፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ወደዚያ ሄዶ ታምራት ቢሠራ ብዙ ሕዝብ ስለሚኖር ድንቅ ሥራውን ተመልክቶ ሊያደንቅና ሊመሰክር ይችላልና ነው:: ኢየሱስ ግን እንዲህ ባለ መንገድ ዝናን ማግኘትን አልፈለገም:: ከወንድሞቹ ጋር ወደ ኢየሩሳሌምም አልሄደም:: ለእርሱ መወደድንም ሆነ መደነቅን ባያተርፍለትም የእግዚአብሔርን መልእክት

ማወጁን አላቋረጠም:: ከቍጥር 2-7 ያለውን ክፍል እናነባለን፤ በተጨማሪም በኢየሱስና በእኛ መካከል ያለውን ሁኔታ በማነጻጸር ገለጻችንን እንቀጥላለ:: ከእርሱ ተቃራኒ በሆነ መልኩ በተለይም ሁኔታዎች ሲመቻቹ፣ ለራሳችን ጥቅም ስንጥር ራሳችንን ለፈተና እናጋልጣለን::

ከዚህ ክፍል ተጨማሪ ጥቅሶችን ማንበብ አያስፈልገንም:: ሆኖም ኢየሱስ ወደ በዓሉ ለመሄድና ራሱን ይፋ ለማውጣት ባይፈልግም ከበዓሉ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ እንደ ነበረ ለአድማጮቻችን መንገር እንችላለን:: እርግጥ ይህን ማድረግ አስቸጋሪ ነበር፤ ምክንያቱም እርሱ አከራካሪ ሰው ስለነበረና በተለያየ ሥፍራ የሚገኙ ሰዎችም ስለ እርሱ የተለያዩ አስተሳሰቦች ስለ ነበሯቸው ነው::

የዝግጅት ክፍላችንን በማጥናትና በማደራጀት በቀላሉ ለመንቀሳቀስ የሚያስችል አንድ ሌላ ዘዴ መከተል አለብን:: ድምፃችንን ከፍ አድርገን የምናነባቸውን ጥቅሶች በቀላሉ ማግኘት እንድንችል በኅዳጉ ላይ የመስመር ምልክት ማድረግ እንዳለብን ቀደም ሲል ጠቁመናል:: ጥቅሶቹን ማጠቃለል ወይም ማለፍ እንችላለን:: በምንባቡ ውስጥ የምናገኛቸውን ቍልፍ ቃላትም በማስታወሻ በመጻፍ ፊንታ ከሥራቸው ልናሠምርባቸው እንችላለን:: ይህን ስናደርግ በስብከት ጽሑፋችን ውስጥ ባዶ ስፍራ እንዲኖረን፥ ዐረፍተ ነገሩን ስናነብ የመጽሐፉን ጠቃሚ ቃላት ማየት ያስችለናል::

ከዚህ በላይ ከ10-13 ያለውን ሐሳብ ስናጠቃልል የሚሰመርባቸው ቃላት «እርሱም ... ሄደ»፥ «በሥውር»፥ «ስለ እርሱም በሕዝቡ መካከል ብዙ ጉምጉምታ ነበር» የሚሉ ናቸው:: ምንባቡ ከማስታወሻዎቻችን ጋር ስለተመቻቸ ሐሳቡን በልበ ሙሉነት በማሳጠርና፥ ልናነበው በመረጥነው ክፍል ውስጥ የሌሉ ጠቃሚ ቃላትን በአጽንዖት ማሳሰብ እንችላለን::

### የበዓሉ አጋማሽ

የስብከቱ ቍልፍ ክፍል የሆነውን ከቍጥር 14-17 ያለውን ጥቅስ በማንበብ እንጀምራለን:: እዚህ ላይ ኢየሱስ ስብከት ሳይጀምር እስከ ሳምንቱ አጋማሽ ድረስ እንዴት እንደ ቆየ እናስገንዝባለን:: በዚህ ጊዜ ቀዝቀዝ ብሎ የነበረው የሕዝቡ ስሜት ይነቃቃና በጋለ ስሜት ማዳመጥ ይጀምራል::

እንደተለመደው ሰዎች ስለ ኢየሱስና ስለ ስብከቱ የተለያየ ግምትና አስተያየት ነበራቸው፤ ሆኖም የእርሱ መልእክት የራሱ ፍልስፍና ወይም ጥበብ እንዳልሆነ ገልጾላቸው ነበር:: ከእግዚአብሔር የተሰጠ መልእክት ነበር:: እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ያስገዙና ፈቃዱን ለመፈጸም የተዘጋጁ ቢሆኑ ኖሮ የክርስቶስን መለኮታዊ ትምህርት በተቀበሉ ነበር:: ችግራቸው የማሰብ ችሎታ ማነስ ሳይሆን የፈቃደኝነት እጦት ችግር ነበር:: ዛሬም ይህን የመሰለ ችግር በብዙ ሰዎች ላይ ጉልቶ ይታያል::

በአድማጮቻችን መካከል ያመኑ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ ያላመኑም ሰዎች ሊገኙ ይችላሉ፤ ስለዚህ ወንጌሉ ልባቸውን እንዲያሸንፍ በዚህ ዕድል ተጠቅመን ተገቢውን ትምህርት መስጠት ይጠበቅብናል:: መጽሐፍ ቅዱስን የጸሐፊውን ትርጉም አዛብቶ አንድ ነገር እንዲል አናስገድደውም:: በየትኛውም ዘመን የተነገረው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ትክክለኛነቱን እንዳይለቅ ነቅተን ልንጠብቀው ይገባል:: የሰዎች ተፈጥሮ በሚያስገርም የሰው ልጆች ዘር÷ ባህልና ዘመን እንዳለ÷ ሳይለዋወጥ እናገኘዋለን፤ ስለሆነም ኢየሱስ በዘመኑ ያገኛቸው ሰዎች ዛሬ ካሉት ሰዎች ጋር ተመሳሳይ ናቸው፤ (ወይም ነቢያት በብሉይ ኪዳን ዘመን ካጋጠሟቸው ሰዎች ጋር ይመሳሰላሉ):: ስለዚህ ኢየሱስ በቁጥር 17 ላይ የተናገረውን የእውነት ቃል በአጽንዖት እንናገራለን፤ እንደዚሁም በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ በሚያጋጥመን የሰው ልጆች የፈቃደኝነት ችግር ላይ ይህንኑ ክፍል አስረግጠን መጥቀስ እንችላለን::

ሰዎቹ ስለ ኢየሱስ ለተናገሩት ቃል ትኩረት ለመስጠት ስንል ከቁጥር 18-24 ያሉትን ጥቅሶች ልናልፋቸው እንችላለን፤ (ባለፈው ምዕራፍ ላይ ስለ ተነጋገርንባቸው ነጥቦች በሰፊው እንደሚናገሩ ባጭሩ አሳስበን እንለፍ):: ሰዎች በኢየሩሳሌም ውስጥ ስለ ኢየሱስ ሲጠይቁና በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ በዐይነ ኅሊና እንዲመለከቱ በሚያስችል አኳኋን በቁጥር 25 ላይ ያለውን ጥቅስ ማንበብ እንችላለን፤ በኢየሩሳሌም የነበሩ ሰዎች ያቀረቧቸውን ጥያቄዎችም «ሰውየው ይህ አይደለምን . . .? ሊሆን አይችልም . . . ? ፈጽሞ ሊሆን አይችልም፤ . . . እናውቃለን . . . ፤» የሚሉ ነበሩ:: ከዚያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝቡ ምን ያህል አርቀው የማይመለከቱና የማያስተውሉ መሆናቸውን ለመግለጽ የራሳቸውን ቃላት ተጠቅሞ የሰጣቸውን መልሶች እናነብና ኢየሱስ የመጣበት ሥፍራ ሰማይ መሆኑን በተናገረበት ጥቅስ÷ በቁ. 29 እንደመድማለን:: እርሱ የመጣው ከእግዚብሔር ዘንድ ነው::

በበዓሉ ላይ ከነበሩ ሰዎች ከፊሎቹ ኢየሱስ በተናገረው ቃል በጣም የተቈጩ ቢሆኑም የተቀሩት ግን በቃሉ አመኑ:: ይህ ነጥብ አድማጮቻችን ስለ ኢየሱስ ገለልተኞች መሆን የማይችሉ መሆናቸውን ለማስረዳት ዕድል ይሰጠናል:: በቁጥር 30 እና 31 ላይ ያሉትን ጥቅሶች ሳናነብ ንጽጽራዊ ማብራሪያ በመስጠት በአጽንዖት ማስረዳት እንችላለን::

ይህን ነጥብ በበለጠ ለመረዳት እንድንችል ከቁጥር 33-35 ያሉትን ጥቅሶች እናንብብ:: የአይሁድ አለቆች ኢየሱስን አስይዘው ለማሠር የጥበቃ ክፍሎችን ወደ ቤተ መቅደስ ላኩ፤ ይህን ለማድረግ ግን ኀይል አልነበራቸውም:: ምክንያቱም በወቅቱ ማንኛውም ነገር በኢየሱስ ቁጥጥር ሥር ስለ ነበረ ነው:: እርሱም የሚሞተው አባቱ የወሰነው ቀን ሲደርስ ብቻ መሆኑንና ከሞትም ተነሥቶ ወደ ሰማይ እንደሚሄድ በተዘዋዋሪ መንገድ ነገራቸው፤ ጠላቶቹ ወደዚህ

ስፍራ መድረስ ስለማይችሉ ሄደው ሊያገኙት አይቻላቸውም:: አለማመን ሰዎችን ወደ ሰማይ ከመሄድ ይከለክላቸዋል የሚለው ለአድማጮቻችን ሊነገር የሚገባ እውነታ ነው::

**የዳስ በዓሉ ፍጻሜ**

የመጨረሻውን ክፍል ስናስተዋውቅ የበዓሉን አፈጻጸም ሁኔታና ውሃውን የማፍሰስ ሥርዓት ተምሳሌትነትን መግለጽ እንችላለን:: በገሃዱ ዓለም የሥነ ፍጥረት ሁኔታ፥ ውሃ ሕይወት እንዲኖር ያደርጋል፤ ኢየሱስ ግን የተሻለ ውሃ ይሰጣል፤ (ቊጥር 37ን ይመ.):: እርሱ የሚሰጠው ውሃ የሰዎችን ውስጣዊ ማንነት የሚለውጥና ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ጥማታቸውን የሚያረካ የሕይወት ውሃ እንጂ እንደ ገሃዱ ዓለም ያለ ተራ ውሃ አይደለም:: ይህን የሕይወት ውሃ ማግኘት የሚችሉትም ፍላጎታቸውን የሚያውቁና ርዳታ ለማግኘት ወደ እርሱ ዘንድ የሚመጡት ብቻ ናቸው:: እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ወሳኙ ሁኔታ የዕውቀት ወይም የምሁራዊነት ጉዳይ ሳይሆን የፈቃደኝነት ጉዳይ ነው፤ ቃሉ «ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ»፤ ይላል::

ከቊጥር 38-39 አንብበን እያብራራን እንቀጥላለን፤ ሰዎች በእምነት ወደ ክርስቶስ ሲመጡ ስለሚለወጡ በሌሎች ሰዎች ላይ እንደታየው ይህ አዲስ ሕይወታቸው ከውስጣቸው ፈልቆ ይወጣል:: ክርስቶስ ለሰው ሁሉ የሚመኘው ይህን የመሰለ በመንፈስ የተሞላ ሕይወት እንደ ሆነ ይህ ምስክር ነው:: በዚህ አጋጣሚ አድማጮቻችንን (ራሳችንንም) ማሳሰብ ያለብን ክርስትና ዝም ብሎ ብቻ ስለ ክርስቶስ የሚያወሳ የእምነት ስብሰባ ሳይሆን ከክርስቶስ ጋር በኅብረት የሚኖርበት ሕይወት መሆኑን ነው:: ይሁን እንጂ በዚህ ሰዓት በዚህ ነጥብ ላይ በሰፊው መናገር አንችልም::

ከዚህ ይልቅ ፈጠን ብለን በዓሉ እንዴት እንደተፈጸመ ወደ ማመልከቱ እናልፋለን:: «ልክ ከቊጥር 25-27 ያለውን ክፍል ባነበብንበት ሁኔታ ከቊጥር 40-42 ያለውን እናነባለን፤ እንደገናም በሚያምኑትና በማያምኑት መካከል ስለተከሠተው ልዩነት እንመለከታለን:: ኢየሱስን በተመለከተ ራሳችንን ገለልተኛ ማድረግ አንችልም::

ኢየሱስን ሊይዙ የሄዱት የቤተ መቅደሱ የጥበቃ ሠራተኞች ባዶ እጃቸውን ወደ አይሁድ ተመለሱ:: የሰጡትን ጠንካራ የምስክርነት ቃል በቊጥር 46 ላይ እናነባለን፤ አድማጮቻችንን የኢየሱስ ቃል እየገባቸው ስለ ሆነ የጥበቃ ሠራተኞች የተናገሩት ሐሳብ እነርሱንም ሳይሰማቸው እንዳልቀረ እናምናለን:: ከቊጥር 47-52 እንደምናነበው የአይሁድን መሪዎች እነርሱም ሳይነቋቸው አልቀሩም፤ እነዚህ መሪዎች ከዕብሪታቸው ብዛት የተነሣ «በኢየሱስ ያመኑት ያልተማሩትና አዋቂ ያልሆኑት ሰዎች ናቸው» ሲሉ ተናገሩ:: በአንጻሩ ከተማሩት

መካከል የሚቈጠሩት እንደ እነርሱ ያሉት አንዳቸው እንኳ በእርሱ አላመኑም:: ይህ አነጋገር የድፍረት አነጋገር ቢሆንም እውነትነት የለውም፤ ምክንያቱም ከመካከላቸው ኒቆዲሞስ ርቱዕ ፍትሕ እንዲሰጡ ተማጥኗቸው ነበር:: ነገር ግን ኒቆዲሞስ ለጠየቀው ጥያቄ መልስ ሳይሰጡ በንቀት አለፉት::

የአይሁድ መሪዎች ዓላማ ክርስቶስን ተወግዶ ማየት እንጂ እውነቱን መርምሮ ማግኘት አይደለም፤ ምክንያቱም በግትርነት በኢየሱስ ላይ ስለተነሡበት አዕምሯቸው እውነትን ለማወቅ ያልተዘጋጀ ነበር:: ለዚህም ኢየሱስ «ሰዎች ለእግዚአብሔር ለመገዛት ከፈቀዱ፥ ብዙም ሳይዘገዩ እውነቱን ይገነዘባሉ» ብሎ የተናገረው ሕያው ማስረጃ ነው፤ (ቊ 17 ይመ.):: ራሳቸውን አሳልፈው ሳይሰጡ ቢቀሩ እውነትን ላለማየት ወይም ላለመቀበል የሚቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ:: ይህ ችግር የሚመጣው ከሰው ፈቃድ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ከመሰለ መንገድ በንስሐ ወደ እምነት እንድንመጣ ይጠራናል:: ያለ ንስሐ፥ ያለመመለስና ያለ እምነት እግዚአብሔር የሚሰጠውን ሕይወት ማግኘት አንችልም::

## ተጨማሪ ሐሳቦች

ምንም እንኳን ምዕራፉ 52 ቊጥሮች ቢኖሩትም ጉባኤው ሠላሳውን ብቻ እንዲያነብ እንጠይቃለን:: የምዕራፉን ፍሬ ነገሮች በሙሉ አዳርሰናል፤ የአድማጮችን ሕይወት የሚነኩትን ጥቅሶች አጠቃቀም አስረድተናል፤ ከሁሉም በላይ ምንባቡ ራሱ በስብከታችን ውስጥ እንዲናገር አድርገናል:: ጸሎታችን ሰዎች ምዕራፉ የሚናገራቸውን ተገንዝበው የታዛዥነታቸውን መልስ መስጠት እንዲችሉ ማድረግ ነው:: ይህን ሁሉ ስብከትና ጸሎት በዚህ አጭርና ለዐይነት በቀረበ ዝግጅት ከሚጠይቀው በላይ በብዙ ቃላትና በታላቅ ስሜት እንፈጽማለን:: ሆኖም ምንጊዜም ቢሆን የስብከታችን አጽንዖት ከእኛ ሳይሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ መምጣት እንዳለበት መርሳት የለብንም::

እንደገናም ዓላማችን በገላጭ ወይም በማብራሪያዊ ስብከት አማካይነት ሕዝብን በእግዚአብሔር ቃል መመገብ ቢሆን የእያንዳንዱን ጥቅስ ትርጉም በማብራራት ጊዜ መውሰድ አይኖርብንም በማለት ራሳችንን እናሳስብ ይሆናል፤ ሰዎች ለዘለቄታው የእኛ ስብከት ሰዎችን በመንፈስ የመገንባት ዓላማ ይኑረን፤ ሰዎች ለዘለቄታው የእኛ ስብከት ጥገኞች እንዲሆኑ ማድረግ ደግሞ የለብንም፤ በዚህ ፈንታ በመንፈስ ተቀስቅሰው የተዘጋጀውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አብረውን በመከታተል እንዲዘልቁና ወደ ቤታቸው ሄደውም በበለጠ እንዲያነቡ መርዳት አለብን:: ይህ ዓላማችን በሥራ ላይ መዋል ከጀመረ ዘለቄታ ያለው፥ ክቡር ሥራ ሠራን ማለት እንችላለን::

## ፲፩

### አዲስ ኪዳንን ማብራራት (2)

#### ሞዴሎች ሳይሆኑ ምሳሌዎች ናቸው

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያቀረብናቸው መጽሐፍ ቅዱስን አጥንቶ ለስብከት የመጠቀም ልምምዶች በተለያዩ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች እንዴት ባሉ ልዩ ልዩ ዘዴዎች መጠቀም እንደምንችል የሚያስተምሩን ምሳሌዎች ናቸው እንጂ ሞዴሎች አይደሉም:: እንዲህ ማለትም በዮሐንስ ወንጌል አማካይነት የቀረበው ምሳሌያዊ መንገድም ይህን ከማሳየት አልፎ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ላሉ ሌሎች ረጃጅም ክፍሎች ላሏቸው መጻሕፍት በዚያው ዐይነት ሊረዳን አይችልም:: የምንጠቀምባቸው የልምምድ መንገዶች ወይም ዘዴዎች ለተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ጥናትና ዝግጅት ሊጠቀሙን ወይም ላይጠቅሙን የሚችሉ ነጥቦች በውስጣቸው ይገኛሉ:: በዮሐንስ ወንጌል አሠራር ላይ የተጠቀምንባቸው መንገዶች አንዳንዶቹ ተመሳሳይ መጠን ባላቸው በሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት እምብዛም ሳይጠቅሙን የሚቀሩ ሲሆኑ በአኪያው ግን በብሉይ ኪዳን ውስጥ ላለ መጽሐፍ አጠቃቀም ሊያገለግሉን ይችሉ ይሆናል::

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት ለመመርመርና ዝግጅትም ለማድረግ የተለያዩ መንገዶችንና ዘዴዎችን ለመጠቀም ባደረግነው ክትትል ለየት ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍትን በምን ዐይነት ስልት መገልገል እንዳለብን ማስተዋል ብቻ ሳይሆን በተጨማሪም በተለያዩ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች የመጠቀም ዘዴዎችንም እንደየሁኔታው ማመቻቸት እንዳለብን ተለማምደናል:: አንድ መጽሐፍ ምንም ያህል ይጠር ወይም ይርዘም፥ ምንም ያህል ይቅለል ወይም ይክበድ፥ እኛ ሁልጊዜ ማሰብ ያለብን ተስማሚ የሆነ መንገድ ፈልገን በዚህ መጽሐፍ መጠቀም መቻል ነው::

ገና ያልሄድንበት ጠቃሚ ክፍል ቢኖር ስለ አንድ የብሉይ ኪዳን ነቢይ ወይም ስለ አንድ የአዲስ ኪዳን መልእክት መነሻ ወይም አመጣጥ ነው:: ምክንያቱም ቀደም ሲል ስለ ኢሳይያስ ባነሣንበት ጊዜ ስለ እርሱ የገለጽንበትን ሁኔታ ስለ ወሰንን በመጀመሪያው ስብከታችን ወይም ገለጻችን ላይ ስለ አለፈው ታሪኩ አልተናገርንም:: የሆነ ሆኖ ምን ጊዜም ቢሆን ርእስ ይዘን ለመናገር በምንነሣበት ጊዜ ስለምንናገረው ወይም ስለምናብራራው ርእሰ ጉዳይ ወደ ኋላ መለስ ብለን የመነሻ ታሪኩን ማስተዋወቅ የግድ ይለናል:: አሁን የምንመለከተው ምዕራፍ ስለ አንድ አጭር የአዲስ ኪዳን መልእክት ይሆናል፤ ይሁን እንጂ እግረ መንገዱን ደግሞ ስለ አንድ መጽሐፍ ታሪካዊ ገጽታ እንዴት አድርገን ለአድማጮቻችን እንደምናብራራ ያመለክተናል:: ለምሳሌ:- መልእክቱን ማን፥ ለማን

እንደ ጳፊና፥ በምንስ ምክንያት እንደ ጳፊ ቀደም ብሎ የሚያውቁ ከሆኑ አሁን የመልእክቱን ሁለመና ይዘት የመገንዘብ ዕድል ይኖራቸዋል። ቀጥለን እንደ ልምምድ ምሳሌ አድርገን የምንወስደው የ1ኛ ተሰሎንቄን መልእክት ይሆናል።

## ዝግጅታችንን ከጊዜው ጋር ማስማማት

በተለያዩ ሁኔታዎች በምንመለከትበት ጊዜ አጫጭሮቹን የአዲስ ኪዳን መልእክቶች (አጫጭሮቹን የብሉይ ኪዳን ነቢያትንም) አዘጋጅተን በተከታታይ በስብከቶቻችን አማካይነት ለትምህርት ለማቅረብ በጣም ቀላል የሆኑ መጻሕፍት ናቸው። እነዚህ መጻሕፍት ጥቂት ምዕራፎች ስላሏቸው በቀላሉ ከቤተ ክርስቲያን መርሐ ግብር ጋር የተስማሙ ይሆናሉ። ለምሳሌ አራት ምዕራፎች ያሉትን መጽሐፍ አዘጋጅተን በአራት ሳምንት ውስጥ አስተምረን እንድንጨርስ እንጠየቅ ይሆናል። ከዚህ ያነሰ ሳይሆን የበለጠ ጊዜም ሊሰጠን ይችል ይሆናል።

በሳምንት አንድ ስብከት እንድናቀርብ ተገምቶ የሐዋርያው ጳውሎስን ሁለት መልእክታት፥ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች አዘጋጅተን ሰብከን ለማጠናቀቅ ስምንት ሳምንታት - ለመጀመሪያው መልእክት አምስት፥ ለሁለተኛው ደግሞ ሦስት ሳምንታት እንዲመደብልን ልናስብ እንችላለን። የተሰሎንቄን መልእክታት ከሌሎች መልእክታት ጋር ስናስተያይ ደግሞ መልእክታቱ አጫጭሮች ናቸው፤ ስለዚህ የሚመደብልን ክፍለ ጊዜ በአጠቃላይ ስድስት ቢሆን ለመጀመሪያው መልእክት አራት፥ ለሁለተኛው ደግሞ ሁለት ክፍለ ጊዜ ይሆናል። በሁለቱም መንገድ፥ በ1ኛ ተሰሎንቄ ላይ የምናቀርበው የመጀመሪያው ስብከት (በከፊል ከሐዋርያት ሥራ የተገኘ ቢሆንም) ከምዕራፍ አንድ ጋር የተዘጋጀ የመልእክቱን አመጣጥ ታሪክ የሚያወሳ ይሆናል። የሚቀጥሉትን ምዕራፎች በአራት ወይም በሦስት ስብከቶች ለማጠቃለል ብናስብ ወይም ባናስብ የምናዘጋጀውን መልእክት ያለአንዳች ችግር በስብከቶቻችን ውስጥ ልናካትት እንችላለን።

የመልእክቱን የመነሻ ገጽታ ወይም የአመጣጥ ታሪክ ለማብራራት በምንሻበት ጊዜ አድማጮቻችን በመልእክቱ ውስጥ ያለውን ሐሳብ ለመያዝ እንዲያመቻቸው ከሐዋርያት ሥራ ወይም ከሌሎች መጻሕፍት ተመሳሳይ ጥቅሶችን ራሳቸው እንዲያነቡ ማሳሰብ አለብን። ይህን አስቀድሞ ማድረግ ምንም እንኳ የስብከቱ ዓላማ የመልእክቱን ታሪክ በዋናነት ማቅረብ ሳይሆን ዓላማውን ማብራራት መሆኑ ቢታወቅም፥ በመክፈቻው ላይ የምናብራራቸውን ጥቅሶች ቁጥር ይቀንስልናል። በመሆኑም በመጀመሪያዎቹ ሁለት ወይም ሦስት የሰላምታ ጥቅሶች ስብከታችንን በመደምደም ፊንታ ሥጋት በሌለበት መንፈስ በመልእክቱ ላይ የምናደርገውን ስብከት መቀጠል ያስችለናል።

ከ1ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ አንድ የተወሰዱ ዐሥር ጥቅሶች ቢኖሩንም ለመልእክቱ አመጣጥ ታሪክ መግለጫ ለመስጠት ብዙ ጊዜ ይኖረናል፤ ሆኖም

ከሐዋርያት ሥራ ባገኘነው ሐሳብ ላይ ዝርዝር ማብራሪያ ስንሰጥ ጊዜ በማሳለፍ ወደፊተና መግባት አይኖርብም:: በዚህ ፈንታ ጊዜያችንን ብዙ ሐሳቦችን በሚሰጡንና ለአድማጮቻችንም ስለ መልእክቱ ግንዛቤ በሚያስጨብጡልን ሌሎች የተሰሎንቄ ክፍሎች ላይ ማዋል የተሻለ ነው:: በዚህ ሁኔታ ጊዜያችንን መጠቀሙ የተቀሩትን የመልእክቱን ክፍሎች ለማብራራት ዕድል እንዲኖረን ያደርጋል::

## ስለ ተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት

የተሰሎንቄን መልእክታት ታሪክ በምናጠናበት ጊዜ የምንጠቀምበት ካርታ ቢኖር መልካም ነው:: አድማጮቻችን የሐዋርያት ሥራ 17÷1ን እንዲያወጡ ከነገርናቸው በኋላ (በካርታው በመረዳት) ሐዋርያው ጳውሎስና ሁለቱ የተልእኮ ሐዋርያት÷ ሲላስና ጢሞቴዎስ ከፊልጵስዩስ ወደ ተሰሎንቄ እንደተጓዙ እንገልጽላቸዋለን:: እነዚህ ስፍራዎች በጥንቷ ግሪክ ሰሜን ትገኝ የነበረችው የመቄዶንያ ከተሞች ነበሩ:: ከዚያም በሚቀጥሉት ሦስት ሳምንታት ስብከት ውስጥ እኒህ ልዑካን እንዴት በምኩራብ ውስጥ እንደሰበኩና እንዴት ብዙ ሰዎች እንደ እመኑ ሐሳቡን ሰብሰብ አደርገን እናብራራለን:: ይህም ወደምናነበው ወደ ቁጥር 5 ያመጣናል:: በዚህ ጊዜ አይሁድ በሐዋርያው ጳውሎስ የአገልግሎት ስኬት ስለ ቀኑ÷ የአካባቢውን ወስላቶች አሰባስበው ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ አረፈበት ወደ ኢያሶን ቤት በመሄድ አደጋ ጣሉ፤ ወስላቶቹ ቤቱን ሲያጠቁ ሐዋርያው ጳውሎስን ግን እንዳላገኙት÷ በዚያ ፈንታም ኢያሶንን ይዘው እየጎተቱና እያንገላቱ ወደ ባለሥልጣናቱ ወሰደው የአይሁድን ዐመፀኞች በቤቱ ያስቀምጣል በሚል ሰበብ መክሰሳቸውን በመግለጽ ወደ ማጠቃለያ ሐሳባችን እንቀጥል:: ኢያሶንን በባለሥልጣናቱ ፊት ካቀረቡት በኋላ ዳግም ይህን የመሰለ ችግር እንዳይፈጽም አስጠንቅቀው በዋስ ለቀቁት፤ (ቊ. 9 ይመ.)::

ኢያሶን ዋስ የጠራበትና ማስጠንቀቂያ የተሰጠበት ምክንያት ሐዋርያው ጳውሎስ ከተማውን ለቆ በተቻለ ፍጥነት እንዲሄድ ነበር:: ሆኖም ሐዋርያውና የሥራ ባልደረቦቹ በምሥጢር አምልጠው ቤሪያ ወደምትባል÷ ሌላይቱ የመቄዶንያ ከተማ ሄዱ፤ (ቊ. 10 ይመ.):: በተደረገው አገልግሎት ብዙዎች ስለ አመኑ አይሁድ ሌላ ረብሻ አስነሡ፤ ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ ሸሽቶ መሄድ ነበረበት:: በዚህ ጊዜ ሸሽቶ የሄደው ወደ አቴና (አቴንስ) ከተማ ነበር፤ ከዚያም ሲላስና ጢሞቴዎስ ዘግየት ብለው ተከትለውት ሄዱ፤ (ቊ. 14-15 ይመ.)::

ምንም እንኳን የሐዋርያት ሥራ የተባለው መጽሐፍ ሐዋርያው ጳውሎስ ያደረጋቸውን ጉዞዎች የሚናገር ቢሆንም ስለ ጉዞዎቹ እንቅስቃሴ ጠቅላላ ዝርዝር መረጃ አይሰጠንም:: በሌላ በኩል ሐዋርያው ጳወሉስ ስላደረጋቸው ጉዞዎች በታሪክ ቅደም ተከተል መሠረት የሚሰጡት መረጃዎች የሉትም:: ስለሆነም መልእክቶቹ ሐዋርያውን የሚጠቅሙትንና ለእርሱ ለየት ብለው የታዩትን ደግሞም በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሌሉትን የጉዞ ነጥቦች ያወሳሉ:: ስለዚህ

የሐዋርያትን ሥራ ከሐዋርያው ጳውሎስ መልእክታት ጎን ለጎን በምናነብበት ጊዜ ስለ ድርጊቶቹ የተሟላ መረጃ ማግኘት እንችላለን::

ለምሳሌ ያህል:- የ1ኛ ተሰሎንቄን መልእክት ስናነብ ሲላስና ጢሞቴዎስ ሐዋርያው ጳውሎስን በአቴና ባገኙት ጊዜ÷ ወዲያው ወደ መጣበት በመቄዶንያ ወደሚገኙት አብያተ ክርስቲያን መልሶ እንደ ላካቸው እንማራለን:: ጢሞቴዎስ ወደ ተሰሎንቄ መሄዱን እናውቃለን፤ ሲላስ ደግሞ ወደ ፊልጵስዮስ÷ ወይም ወደ ቤርያ እንደ ሄደ እንገምታለን:: በዚህ ደረጃ ላይ ሳለን አድማጮቻችን የመጸሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን÷ ማመሳከሪያዎችን እንዲመለከቱ አንጠይቃቸውም፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደሚፈለጉት ጥቅሶች እንደምንመለስ ብቻ እንነግራቸዋለን::

እስከዚህ ድረስ ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌልን መስበክና ማስፋፋት አስቸጋሪ የነበረባትንና ጥቂት ሰዎች ብቻ ያመኑባትን የአቴናን ከተማ ለቆ መሄዱን በጥቂት ዐረፍተ ነገሮች እናስታውሳለን፤ ከዚያም አድማጮቻችን የሐዋርያት ሥራ 18÷1 እንዲያነቡ እናሳስባቸዋለን፤ አያይዘንም ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ እንዴት እንደ ሄደ ካሳሰብን በኋላ በዚያ በነበረበት ጊዜ ስለ አጋጠመው የሥራ ስኬት አሳጥረን እናስታውሳለን:: በመቀጠልም ሲላስና ጢሞቴዎስ ከመቄዶንያ ተነሥተው ወደ ቆሮንቶስ በመሄድ÷ በዚያ ስለ ነበሩ አብያተ ክርስቲያን ለሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ነገሩት የሚጠቁመንን ቊጥር 5ን እናነባለን:: በዚህን ጊዜ ጢሞቴዎስ ከተሰሎንቄ ይዞት የመጣው ዜና ሐዋርያው ጳውሎስን ቀሰቀሰውና ዛሬ 1ኛ ተሰሎንቄ የምንለውን መልእክት ጻፈ፤ ቀጥሎ ያለው ተግባራዊ ማብራሪያ የሚያተኩረው በዚህ መልእክት ላይ ይሆናል::

**ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፈው**

አሁን ተግባራዊ ማብራሪያዎችን ለማድረግ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች መልእክት የምናመራበት ዋናው ዓላማ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተማርነው ትምህርት ከዚህ መልእክት ጋር እንዴት እንደሚግባባ ለአድማጮቻችን ለመግለጽ ነው:: ስለዚህ ማብራሪያቻችንን ከመጀመራችን በፊት ከዚሁ መልእክት ውስጥ አራት ምርጥ ጥቅሶችን እንመለከታለን:: ምንም እንኳን ስለዚህ ለአድማጮቻችን ባንናገርም የሐዋርያው ጳውሎስን መልእክቶች መገንዘብ እንዲችሉ አስቀደመው የሐዋርያት ሥራን ታሪክ እንዲያውቁ ማድረግ ጠቃሚ ልምምድ ይሆናል::

የምናስተምራቸው ሰዎች የተሰሎንቄን መልእክት እንዲያወጡ በምንነግራቸው ጊዜ የሚከፍቱት ያለ አንዳች ጥርጥር የመጀመሪያውን ምዕራፍ ነው:: እኛም ወዲያው ማድረግ ያለብን የመጀመሪያውን ጥቅስ ለአጭር ጊዜ እንዲያነቡ ማድረግ ነው:: ይህ ጥቅስ በሐዋርያት ሥራ 18÷5 ላይ ያነበብነውን ፍሬ ሐሳብ ይነግረናል፤ ያም ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን መልእክት በጻፈበት ጊዜ ሲላስና ጢሞቴዎስ አብረውት በቆሮንቶስ ውስጥ መኖራቸውን ነው:: ብዙ ሰዎች

ሐዋርያው ጳውሎስ ለመልእክታቱ መክፈቻ ያደረጋቸው ጥቅሶች የሚስቡ ሆነው አይገኙላቸውም። ሆኖም አንድ የሚስብና ጠቃሚ የሆነ ነጥብ ከጠቀስን በኋላ ወዲያውኑ ወደ ሌላ ክፍል እናልፋለን። ከዚያም አድማጮቹ ወደ ምዕራፍ 2 ቁጥር 17-18 ወዳለው እንዲያመሩ እንነግራቸዋለን።

በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ተሰሎንቄ ተቻኩሎ መሄዱን ይጠቁማል። እዚህ ላይ ሐዋርያው በዚህ ሁኔታ በመሄዱ ምክንያት በተሰሎንቄ ውስጥ ካሉ አንዳንድ ሰዎች ራስ ወዳድና ድፍረት የሌለው ብለው እንደ ከሰሱት ጢሞቴዎስ ነገረው። አብልጦ ስለ ራሱ የሚያስብና ስለ እነርሱ ግድ ያልነበረው ሰው አድርገው አቅርበውታል። በዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ በመለሰው መልስ ልቡ የተሰበረ ይመስላል። ከእነርሱ በሚለይበት ጊዜ ይሰማው የነበረው ኀዘን ልክ ከሥጋ ዘመዶቹ ሲለይ የሚሰማውን ያህል ነበር። ነገር ግን በመንፈስ ከእነርሱ የተለየ አልነበረም። እነርሱን ለማየት በጣም ይናፍቅና ሊያያቸውም ደጋግሞ ሞክሮ ነበር፤ ሄዶ እንዳያያቸው ግን ሰይጣን አዘገየው። በሚቀጥሉት ስብከቶች ውስጥ ሊጠቃለሉ የሚችሉትን ፍሬ ነገሮች ልብ በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ስለ ነበረው ፍቅርና በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም ረገድ ስለ ነበረው ደስታ አጽንዖት ሰጥቶ ለማስተማር ከቁ. 19-20 ድረስ ያለው ይነበብ።

እነዚህ ጥቅሶች በአስተሳሰብም ሆነ በስሜት ላይ መፍረድ ስለሚኖረው አደጋ መጋቢያዊ አስተያየትን ለመሰንዘር ዕድል ይሰጡናል። ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ተሰሎንቄ መመለስ አለመቻሉ እንደ ፍርሀት ወይም ፍላጎት እንደ ማጣት የሚቈጠርበት ሁኔታ አይደለም። ምናልባት ኢያሶንን ዋስ ጠርቶ የተለቀቀበት ሁኔታ ወደ ተሎንቄ እንዳይመለስ አድርጎት ይሆናል። ዝርዝር ሁኔታውን ማወቅ አንችልም፤ ሰይጣን በእግዚአብሔር አገልጋዮች ፊት የተለያዩ ዕንቅፋቶችን እንደሚያደርግ ግን እናውቃለን። በዚህ ነገር ላይ ትኩረት ያለው ትምህርት ለምእመናን ለመስጠት እንድንችል ተግባራዊ በሆነ ምሳሌ መጠቀም አለብን።

ሌላው ትኩረት የሚሰጠው ነጥብ የሚሰናዳው በሚቀጥሉት ጥቅሶች ውስጥ ሲሆን እነርሱም በምዕራፍ 3 ከቁ. 1-2 ላይ ይገኛሉ። አንዳንድ ሰዎች በቀላሉ ተስፋ ይቈርጣሉ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ግን እንዲህ ያለ ሰው አልነበረም። ያኔ ወደ ተሰሎንቄ መመለስ ባልቻለበት ጊዜ ዝም ብሎ እያጕረመረመ ወይም ተስፋ ቈርጦ ቁጭ አላለም፤ ቀጥሎ ቈራጥ የሆነ እርምጃ በመውሰድ ጢሞቴዎስን በእርሱ ፈንታ ላከው።

በተመሳሳይ ሁኔታ ሰይጣን በመንገዳችን ላይ ዕንቅፋቶችን ቢደረድርም ተስፋ መቍረጥ የለብንም። ከዚህ ባሻገር በብሩህ ተስፋ ወደ ፊት መመልከት ዕንቅፋቶችን ሁሉ አሽቀንጥረን የምንጥልበትንና የምናሸንፍበትን መፈለግ አለብን። ዕርግጥ ይህንን ለማድረግ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ውድ የሆነ ዋጋ በግላችን መክፈል ይኖርብናል። በዚህን ወቅት የሐዋርያው ጳውሎስን ሁኔታ ብናስብ

የቅርብ አጋሮቹ የነበሩትን ሲላስንና ጢሞቲዎስን መልሶ ወደ መቄዶንያ በሚመልሳቸው ጊዜ ደጋፊዎቹን ካጠገቡ አጥቷል። ስለሆነም በአቴና የነበረውን ችግር ራሱ መሸከም ወይም መወጣት ነበረበት። ከቍጥር 1-2 ያለውን ምንባብ ቀደም ሲል በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 17 ላይ የተመለከተውን ሐቅ ያረጋግጥልናል። ሐዋርያው ጳውሎስን ያጋጠመው እውነታ እኛንም ዛሬ ያጋጥመናል። ይህም በሌሎች ስም የሚደረግ አገልግሎት የሚኖረንን ምርጫና ምቾት በመሥዋዕትነት ማቅረብ የግድ ይለናል።

ከቍጥር 3-5 ባለው ክፍል ላይ የምንሰጠውን ማብራሪያ መቀጠል እንችላለን። ይህም እንደገና በሚቀጥሉት ስብከቶች ውስጥ ምን ያህል ጥቅሶቹን ማካተት እንዳለብን በምናደርገው ግምት ላይ የተመሠረተ ይሆናል። እነዚህን የጥቅስ ምንባቦችና ማብራሪያ የምንደመድመው በሐዋርያት ሥራ 18÷5 ጋር ግንኙነት ያለውን የቍጥር 6ን ጥቅስ አድማጮቻችን እንዲያነቡ በማሳሰብ ይሆናል። አሁን ጢሞቴዎስ ከተሰሎንቄ ተመልሶ ሐዋርያው ጳውሎስን በቆሮንቶስ ያገኘውና የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ከጥንካሬ ወደ ጥንካሬ መሸጋገሯን ያጫውተዋል። ሐዋርያው ጳውሎስም በዚህ መልካም ዜና ደስ ስላለው ቀጥለን የምናነበውን መልእክት ለመጻፍ ቁጭ አለ።

## ሌሎች ልናውቃቸው የሚገቡ ጉዳዮች

አሁን በምዕራፍ አንድ ላይ ማብራሪያ ለመስጠት ተዘጋጅተናል፤ ከዚያ በፊት ግን ጢሞጤዎስ ከተሰሎንቄ ስለ አመጣው ሌላ ዜና ባጭሩ የምናወሳቸው መሆናችንን ለአድማጮች እንነግራቸው ይሆናል። ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን በሚቃወሙ መናፍቃን ቡድን ሥር ነበረች፤ እንደዚሁም ራስ ወዳድ በሆኑ÷ ሐዋርያው ጳውሎስን በውሸት በሚከሱ ጥቂት ሰዎች ተቸግራ ነበር። ደግሞም ጥቂት ሰዎች በክርስቲያን ደረጃ ሊኖር የሚገባው የሞራል ብቃት አልነበራቸውም። ሌሎቹ ደግሞ በሥራቸው ሰነፎችና የሌሎችን ችሮታ በማይገባ ሁኔታ የሚጠብቁ ነበሩ። ከዚህም በስተቀር የክርስቶስን ዳግም መምጣት በተመለከተና ከሌሎች ጉዳዮች ላይ የግንዛቤ እጥረት ይታይባቸው ነበር።

እነዚህን ነጥቦች ወደሚናገሩት ጥቅሶች መሄድ አያሻንም፤ ምክንያቱም ጥናታችንን እየቀጠልን ስንጓዝ ወደ ኋላ ላይ እንደርስባቸዋለንና ነው። ሆኖም አድማጮቻችንን ወደ ፊት ለሚሆነው ሁሉ ግራ እንዳይጋቡና ዝግጁ እንዲሆኑ አደርገናቸዋል ማለት ነው። የያኔዎቹን የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ያጋጠሟቸው ችግሮች የዛሬዎቹን ክርስቲያኖች ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች ጋር ተመሳሳይ መሆናቸውን እንገልጻለን። ሐዋርያው ጳውሎስ ለእነዚህ ሰዎች የተናገረውን በምናስብበት ጊዜ እግዚአብሔር ለእኛ የሚናገረውንም ማሰብ እንችላለን።

## ከመነሻ ታሪክ በበለጠ

በተሰሎንቄ መልእክት ላይ የምናዘጋጀው የመከፈቻ ስብከት፥ ከሁለቱ የመጀመሪያ ምዕራፎች ርዝመት አለመመጣጠን የተነሣ ዕቅዳችን ከተለመደው አዘገጃጀት ትንሽ ለየት ይላል:: ምዕራፍ አንድ አመቺ በሆነ ስፍራ ላይ ያበቃል፤ (ይህም ምዕራፍ 10 ቍጥሮች አሉት፤ እዚያ ላይ ያቆማል):: ምዕራፍ ሁለት የሚያበቃው ግን በ16ኛው ቍጥር ላይ ነው:: እዚህ ቍጥር ላይ ሳይደርስ ምዕራፉ አይደመደምም:: ስለዚህ እኛ ስለ ተሰሎንቄ የምናደርገው ታሪካዊ ማብራሪያ ወይም የአመጣጥ ታሪክ ወደ ዐሥር ደቂቃ ገደማ ይሆናል:: እንዲህ ማለትም ወደ ምዕራፍ 2 የመደምደሚያ ቍጥር 16 ለመድረስ ብንፈልግ ሁለቱን ምዕራፎች ለማጠቃለል ቶሎ ብለን ከሃያ ደቂቃ በማይበልጥ ጊዜ መጠቀም ይኖርብናል:: ሁለቱን ምዕራፎች ለመሸፈን በምናደርገው የመግቢያ መግለጫና የጥድፊያ ማብራሪያ ስብከት በሠላሳ ደቂቃ ውስጥ ብዙ ነገር ማካተት እንድንችል አድርገን ራሳችንን ውጥረት ላይ እንጥላለን::

በሌላ በኩል በመክፈቻው ስብከታችን ውስጥ ከምዕራፍ አንድ አልፈን ሰፋ አድርገን ለመናገር ብንወስን በሚቀጥሉት ስብከቶች ውስጥ የምንሰብካቸውን ፍሬ ነገሮች መጨመር ሊኖርብን ነው:: ስለዚህ ስብከታችንን በምዕራፍ አንድ ላይ ለመጨረስ እንወስናለን:: ግን በመክፈቻው የመልእክቱ ታሪክ ላይ ከሌሎች ምዕራፎች ወስደን እንጨምራለን:: ይህ አዘገጃጀት ሁለት ጥቅሞች አሉት፤ የመጀመሪያው ጥቅም አድማጮቻችን ስለ መጽሐፉ የተሻለ ስሜት እንዲኖራቸው ያደርጋል፤ ሁለተኛ በተለይ ቀደም ሲል ማብራሪያ የተሰጠባቸውን ክፍሎች ባጭሩ ነካክተን ለማለፍ ጊዜ ይሰጠናል:: በሌላ አነጋገር ስለ መልእክቱ ታሪካዊ አመጣጥ የምናደረገው ማብራሪያ፥ ከቍርጥራጭ ማስረጃዎች በላይ ክብደት ይኖረዋል:: ጠቃሚ በሆኑ ክፍሎች ላይ ማብራሪያዊ መግለጫ ያለው ከመሆኑም በላይ ተግባራዊ ጠቀሜታም ይዞ የቀረበ ይሆናል:: ምንም እንኳን ስብከታችንን በምዕራፍ አንድ ላይ ብንደመድምም የአድማጮቻችንን ግንዛቤ ወደ መጽሐፉ ውስጥ እንዲደርስ እናደረጋለን::

## እውነተኛ ክርስቲያንነት

ምዕራፍ 1 ቍጥር 2 እና 3ን በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ እምነት፥ ተስፋና ፍቅር ያስተማረውን አድማጮቻችን ልብ እንዲሉ በማሳሰብ እንጀምራለን:: ሆኖም ሐዋርያው ጳውሎስ በሰጠን ጠቃሚ የተዋጽኦ ሐሳብ ላይ በመመሥረት ያልተሟላ ስብከት እንዳናደርግ መጠንቀቅ አለብን:: ሐዋርያው ጳውሎስ በጸለየባቸውና በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ በተመለከታቸው መልካም ፍሬዎች ላይ ማብራሪያ መስጠት እንችላለን፤ ሆኖም ወደ ፊት መቀጠል ይኖርብናል:: ሁለት ዐበይት ነጥቦችን አጒልተን በማሳየት በመግቢያችን ላይ ባቀረብነው የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ላይ ዕውቀታችንን ለመመሥረት እንፈልጋለን:: ስለ

እውነተኛ እምነት የሚናገረው ይህ የመጀመሪያው ክፍል የሚገኘው ከቍጥር 4-7 ባለው ነው። ሁለተኛው ደግሞ የሚናገረው ለአገልግሎት ስላለው ፍላጎት መነሣሣት ሆኖ የሚገኘው ከቍጥር 8-10 ድረስ ባለው ክፍል ነው።

አንደኛው የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች የእምነት ጽናት ማስረጃ ለወንጌል ብርቱዎች ሆነው የመቆማቸው ሁኔታ ነበር። ስለዚህ ወንጌልን እንደ ልዩ ፍልስፍና አድርገው የተቀበሉ ሳይሆኑ ቃሉን የተቀበሉት ከእግዚአብሔር እንደተላከና ሕይወት የመለወጥ ኀይል እንዳለው መልእክት አድርገው ነው። እምነታቸው የተገኘው ከሰባኪዎቹ የሚስብ አነጋገርና ቃላት ሳይሆን ልባቸውን በእግዚአብሔር እውነት ከመገበው ከመንፈስ ቅዱስ ነው። ሆኖም እዚህ ላይ ሰዎቹ በአካሄዳቸው የሚሰብኩትን የመልእክቱን የእውነት ቃል እየኖሩ ስለሚመሰክሩ በዚህ ረገድ ላላቸው አስተዋጽኦ የላቀ ነው። ይህ ሁሉ ከቍጥር 4-5 ድረስ ባለው ክፍል የተገለጸ ከመሆኑም በላይ ዛሬ በሰባኪዎችና በምእመኑ ላይ እንዴት አድርገን እንደምንተገብራቸው ትምህርት ይሰጡናል።

ስለ እውነተኛ እምነት ተጨማሪ ነጥብ በቍጥር 6-7 ድረስ ተነግሯል። ሐዋርያው ጳውሎስ በተሰሎንቄ ውስጥ በሰበከ ጊዜ ስብከቱን ያደመጡ ሰዎች የደረሰበትን ተቃውሞ ተመልክተዋል። እርሱም በአጸፋው ሲናገር እነርሱም በወንጌል በሚያምኑበት ጊዜ ይህንኑ የመሰለ ተቃውሞ እንደሚያጋጥማቸው አረጋግጦላቸዋል። ስለሆነም ሰዎች አዳማዊ የሆኑ ነገሮችን በሚቀበሉበት አልባሌ መንገድ ወንጌልን ለመቀበል እንዳይሞክሩ አስጠንቅቋቸዋል። ከዚህ የተነሣም ሰዎች ላሰማው ስብከት የሐሰት ስሜት ምላሽ መስጠት አልቃጡም ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ ቀደም ሲል ራሱን ምሳሌ አድርጎ ስላሳያቸው ግልጽ አድርጎ ስለ ተናገራቸው ወንጌልን ቢቀበሉ ምን እንደሚደርስባቸው አውቀው ነበር፤ (ምዕራፍ 2፥2-3 ያለውንና እንዲሁም ከምዕራፍ 3፥3-4 ያለውን ይመ.)። ሕይወታቸው የስደት ሕይወት ቢሆንም በዚህ የፈተናቸው ወቅት ያሳዩት ደስታ ለሌሎቹ ክርስቲያኖች መልካም ምሳሌን አድርጎ አቅርቧቸዋል። ዳግም የሐዋርያው ጳውሎስን ቃል በምናብራራበትና በተግባር ላይም በምናውልበት ጊዜ በሰፊው ልናስብባቸው የሚገቡና በተግባር ላይ ለማዋልም የምንገደድባቸው አያሌ ፍሬ ነገሮች ይኖራሉ።

## መነሣሣትና በፍላጎት ላይ የተመሠረተ የወንጌል ስርጭት

የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ምሳሌነታቸው በስደት ምክንያት ሳይፍረከረኩ በእምነታቸው መጽናታቸው ብቻ ሳይሆን ወንጌልን ለማሰራጨት በነበራቸው ተነሳሽነትና ልባዊ ፍላጎትም ጭምር ነበር፤ (ቍጥር 8 ይመ.)። አንዳንድ ጊዜ ጸንቶና ብርቱ ሆኖ መቆም እንደ መከራና ችግር ያሉትን መቋቋም የእሉታዊ አስተሳሰብ ስሜት ይሰጠዋል፤ ለተሰሎንቄ ምእመናን ግን ይህ ሁኔታ አወንታዊ ነበር። ስለሆነም ለመከላከል ብለው ቀጥ ብለው ባሉበት ስፍራ ሳይቆሙ ወይም

ወደ ኋላ ሳይሸሹ ወደ ፊት ቀጠሉ። በዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያናቸውን የወንጌልን ተልእኮ በአካባቢው ሊያስፋፉ ቻሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ስለ መሰለው የተሰሎንቄ ምእመናንን ብርታትና ጽናት አጋኖ መናገር አልፈለገም፤ ምክንያቱም ጥረታቸውን ሁሉ ሰው ቀደም ሲል አውቆት ነበርና ነው። ስለሆነም የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያንን ለአባላቱ ጥቅምን የምታመጣ ክበብ አድርገው ሊቆጥሯት አልፈለጉም። በዚህ ፈንታ ቤተ ክርስቲያናቸው የጠፉትን የምትፈልግ፥ መንፈሳዊ ረሀብ ያለባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች በእግዚአብሔር የሕይወት መልእክት የሚረኩባት ተቋም አድርገው ቈጥረዋት ነበር።

ሁላችንም ብንሆን ከተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ሕይወትና ተግባር በርካታ ምሳሌነት ያለው ትምህርት መቅሰም እንችላለን። ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ መልእክት ውስጥ ጽፎ ከተወልን ትምህርት በመነሣት ለራሳችንም ሆነ ለምነሰብከው ሕዝብ የምንለው ይኖረናል። ራሳችንን በዚያ በመጀመሪያው መቶኛ ክፍለ ዘመን ከነበሩ ክርስቲያኖች ጋር ስናነጻጽር ኀፍረት ይሰማን ይሆናል፤ ሆኖም የምናስተምራቸው አድማጮቻችን በዚህ ተደናግጠው እንዳያፈገፍጉ መጠንቀቅ ደግሞ ይኖርብናል። ይህ ምዕራፍ ሐሳቡን የሚቋጨው ከፍ ያለ ተልእኮ ባለው ሁኔታ ነው፤ የእኛም ስብከት ተመሳሳይ መደምደሚያ ሊኖረው ይገባል።

ከቍጥር 9-10 ያለውን ክፍል አንብበን በምናብራራበት ጊዜ ሐዋርያው ጳውሎስ በእነዚህ አማኞች ዘንድ ስለታየው መለወጥ ሲናገር እናገኘዋለን። ቀድሞ ሕይወት ያልነበረው የጣዖት ተገዢዎች የነበሩ እነዚህ ሰዎች አሁን ግን የሕያው አምላክ አገልጋዮች ሆነዋል። ምንም አንኳን ስደት ቢደርስባቸውም የተነሣው ሕያው የሆነው የክርስቶስ ሕይወት ተሳታፊዎች ናቸው። ከእርሱ ጋር ስለ ተሰቃዩ ከእርሱ ጋር ይነግሣሉ። ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ክርስቶስ ዳግም ተመልሶ በመምጣት ለእነርሱ ብቻ ሳይሆን የእርሱን መገለጥ ለሚጠባበቁት ሁሉ አክሊሉን የሚሰጥበትን ጊዜ በደስታ ይጠባበቃሉ፤ (2 ጢሞ. 4፥8)።

# ፲፪

## የትምህርቱን መርሐ ግብር ማዘጋጀት

### የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተግባር

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሆንን፥ እግዚአብሔር የሰጠንን ቤተ ክርስቲያን የመንከባከብና የመመገብ ኀላፊነት አለብን:: መሪዎች መንጋውን የሚንከባከቡና የሚጠብቁ ባለ ዐደራ እረኞች መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ በምሳሌ ይናገራል፤ (ዮሐ. 21፥15-17፤ የሐ. 20፥28 ፤ 1ጴጥ. 5፥1-4)::

በዚህ ተምሳሌት በቀረበው አጽንዖት ኀላፊነቱ ያለው በመንጋው ላይ ሳይሆን በባለዐደራዎች ላይ ነው:: መንጋውን ተገቢ የሆነ ምግብ መመገብና መንከባከብ አለብን:: አንድ ሌላ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ከቃሉ ያካፍላል፥ ወይም አንድ ቀን ተገቢ የሆነ ስብከት እንድንሰብክ ልዩ ዕድል ይመጣልንል ይሆናል ብለን ከኀላፊነት መሸሽ አይገባንም:: እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን እንድንመግብ ዐደራ ሰጥቶናል፤ ይህን ኀላፊነት በሚገባ ለመወጣት በዕቅድ መሥራት የግድ ይለናል:: መልካም ወላጆች ለልጆቻቸው ምግብ ማግኘትን ቀላል ተግባር አድርገው እንደማይመለከቱት ሁሉ መልካም እረኞችም መንጋውን የመመገብን ሥራ ቀላል አድርገው መመልከት የለባቸውም::

ሐዋርያው ጳውሎስ በአንድ ወቅት ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመመገብ ኀላፊነታቸውን ሲያስገነዝባቸው እርሱ ራሱም እንዴት ይመግባቸው እንደ ነበረ አሳስቧቸዋል:: ይህን ባደረገበት ጊዜም ስለ እግዚአብርሔር ሙሉ ዐላማ አስተማራቸው፤ እኛም ፈለጉን እንድንከተል ምሳሌነቱን ትቶልናል፤ (ሐዋ. 20፥27-28):: እግዚአብሔር በሁሉም ዘርፍ የሰጠንን መገለጥ በሚያጠቃልል መልኩ ቤተ ክርስቲያንን ሚዛናዊ ትምህርት መመገብ በምንችልበት አካሄድ ልንሠራ ይገባናል:: ይህም ስብከታችንን በተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት፥ በነገረ መለኮት አስተምህሮ፥ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮችና ጠቅላላ ዝግጅታችንን በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ በመመሥረት የምንፈጽመውን ተግባር ያካትታል:: ዐላማችን የሚያተኵረው ዕውቀትን በማስተላለፍ ዘዴ ላይ ብቻ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያንን አመጋገብም ትኵረት በማድረግ ላይ ነው::

### ለየትኛዋም ቤተ ክርስቲያን በየትም ሥፍራ

ብዙ ጊዜ መርሐ ግብሮችንንና የጊዜ ሰሌዳዎችን በማዘጋጀት ረገድ ችግር አለብን:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደ መረጃ ያቀረብነው መርሐ ግብር ቤተ ክርስቲያንን ሚዛናዊ በሆነ ትምህርት ለመመገባችን እርግጠኞች እንደንሆንን

ያግዘናል:: መርሐ ግብሩን የምንመለከተው እንደ መነሻ፥ ምሳሌ እንጂ እንደ ቋሚ መመሪያ አይደለም:: ቤተ ክርስቲያን በሚያመቻት ሁኔታ ልትለዋውጠውና ልታዘጋጀው ትችላለች፤ ለብዙ ዓመታት በተለያዩ አገሮች በሚስማማ ሁኔታ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ ውሏል::

የየሳምንቱን ክንዋኔ ስንመለከት የአንዱ ቤተ ክርስቲያን መርሐ ግብር ከሌላው የተለያየ ነው:: ስለሆነም ይህ የመርሐ ግብር ንድፈ ሐሳብ የሁሉንም ቤተ ክርስቲያን ተግባራት ይሸፍናል ብለን አናስብም:: መርሐ ግብሩ የተነደፈው በየጊዜው አንድ ዓመትን እንዲሸፍን ተደርጎ ነው፤ ዓመቱም በአራት ሩብ ተከፋፍሎ ተመድቧል:: እያንዳንዱ ሩብ ዐሥራ ሁለት ሳምንታት እንዲኖረው ሲደረግ አንድ ነጻ ሳምንት ብቻውን ይቀራል::

በየሳምንቱ ሁለት ስብከቶች ይደረጋሉ፤ በዚህ ሐሳብ ስንሄድ በአንድ ሩብ ውስጥ አሥራ ሁለት ስብከቶች ይቀርባሉ:: (ፕሮግራሙ የቡድን ጥናቶችን፥ ውይይቶችን፥ በአትሮንስ ላይ የሚቀርቡ ስብከቶችን ስለሚያካትት «በስብከት» ፈንታ «ንግግር»፥ «በአገልግሎት» ፈንታ «ስብሰባ»፥ «በመስበክ» ፈንታ «ማስተማር» ልንለው እንችላለን):: በየሳምንቱ ከሚደረጉ ሁለት ንግግሮች አንዱ በመደበኛው የቤተ ክርስቲያን አምልኮ ሥነ ሥርዓት ላይ ይቀርባል፤ ይህም ስብሰባ 1 ይባላል:: ሌላው ሳምንታዊ ንግግር (ለምሳሌ ቤተሰብ፥ ወንጌል ሥርጭት፥ የማስተማር አገልግሎት፥ ማለዳም ሆነ ምሽት ላይ ቢደረግ) 2ኛው የእሑድ አገልግሎት ወይም የሳምንቱ አጋማሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይሆናል፤ ይህ ስብሰባ 2 ተብሎ ይመደባል:: መርሐ ግብሩን ልናሰፋው፥ ልናጠበው፥ ለጥቂት ወይም ለብዙ ስብሰባዎች ልንጠቀምበት እንችላለን፤ ነገር ግን ለ12 ሳምንታት (ለ24 ንግግሮች) ለመነሻነት እንዲጠቅም የተዘጋጀ ዕቅድ ነው::

አንዳንድ መጻሕፍት ወይም ርእሶች ለስብሰባ 1 ሲጠቅሙ ሌሎች ደግሞ ለሰብሰባ 2 ይጠቅማሉ:: ይህ ሁሉ በስብሰባው አካሄድ ስልትና በሚሳተፉት ሰዎች ሁኔታ ላይ የተደገፈ ነው:: ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስና ክርእሱ ጋር የተዛመዱት ርእሶች በሚገባ ከቀረቡ ክርስቲያኖች ወይም ሌሎች፥ ሁለቱም ጥቅም ሊያገኙበት ይችላሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ በሚገባ ተብራርቶ ትምህርቱ ከተሰጠ የሰዎችን ልብ ይነካል:: ያደመጡት መልእክትም ከዛሬው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በምን አኳኋን እንደሚዛመድ በግልጽ ሊረዱት ይችላሉ::

መርሐ ግብር ለአሠራር የሚረዳ ቢሆንም የምናተኩረው በማስተማሩ ጥረት ላይ ነው:: ስለሆነም አንድ መርሐ ግብር የማስተማር ጊዜን ከማመልከት በላይ ዘልቆ አይሄድም:: ትምህርቱ ጥቅም እንዲኖረው አድርጎ የማቅረብ ጉዳይ በስፋት የሚመለከተው ትምህርቱን የሚሰጡትን ሰዎች ነው:: ተስማሚ መምህራን በሌሉበት ስፍራ መረሐ ግብር ቤተ ክርስቲያን በወቅቱ ከምትሰጠው አገልግሎት የበለጠ እንድታደርግ አያስገድዳትም አብዛኞዎቹ በተ ክርስቲያኖች ከስብሰባ 1 እና 2 ጋር እቻ የሆነ መርሐ ግብር አላቸው::

| ዕቅድ - ሀ - | | | |
|---|---|---|---|
| ፩ኛ ሩብ | ብ.ኪ. | ኢያሱ፥ መሳፍንት፥ ሩት | 6 ንግግሮች |
| | | መዝሙረ ዳዊት | 6 |
| | አ.ኪ. | የሐዋርያት ሥራ | 6 |
| | ወቅታዊ ርእስ | ቤትና ኅብረተ ሰብ | 6 |
| ፪ኛ ሩብ | ብ.ኪ. | ምሳሌ | 6 ንግግሮች |
| | አ.ኪ. | ሮሜ | 12 |
| | ወቅታዊ ርእስ | ቤተ ክርስቲያንና የወንጌል ተልእኮ | 6 |
| ፫ኛ ሩብ | ብ.ኪ. | ኤርምያስ፥ ሰቆቃወ ኤርምያስ | 12 |
| | አ.ኪ. | የማቴዎስ ወንጌል | 6 |
| | ወቅታዊ ርእስ | የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን | 6 |
| ፬ኛ ሩብ | ብ/ኪ. | ዘፍጥረት | 6 ንግግሮች |
| | አ.ኪ. | ኤፌሶን | 6 |
| | | 1ኛና 2ኛ ጴጥሮስ ፥ ይሁዳ | 6 |
| | ወቅታዊ ርእስ | እግዚአብሔር | 6 |

| ዕቅድ - ለ - | | | |
|---|---|---|---|
| ፩ኛ ሩብ | ብ.ኪ. | 1ኛና 2ኛ ነገሥት፥ ዜና መዋዕል | 12 ንግግሮች |
| | አ.ኪ. | ዮሐንስ 1-12 | 6 |
| | ወቅታዊ ርእስ | ክርስትያናዊ ሕይወትና አገልግሎት | 6 ንግግሮች |
| ፪ኛ ሩብ | ብ.ኪ. | ኢሳይያስ 1-39 | 6 |
| | አ.ኪ. | 1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስ | 12 |
| | ወቅታዊ ርእስ | የቤተ ክርስቲያን ታሪክ | 6 |
| ፫ኛ ሩብ | ብ.ኪ. | ሕዝቅኤል | 6 ንግግሮች |
| | | ሆሴዕ ፥ ኢዩኤል | 6 |
| | አ.ኪ. | የማርቆስ ወንጌል | 6 |
| | ወቅታዊ ርእስ | ኀጢአትና ድነት | 6 |
| ፬ኛ ሩብ | ብ.ኪ. | ዘፀአት | 6 ንግግሮች |
| | አ.ኪ. | ቆላስያስ፥ ፊሊሞና | 6 |
| | | 1ኛ፥ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ | 6 |
| | ወቅታዊ ርእስ | የክርስቶስ ማንነትና ሥራው | 6 |

| ዕቅድ - ሐ - | | | |
|---|---|---|---|
| ፩ኛ ሩብ | ብ.ኪ. | 1ኛና 2ኛ ሳሙኤል | 6 ንግግሮች |
| | | መዝሙራት | 6 |
| | አ.ኪ. | የአዲስ ኪዳን አመጣጥ ታሪክ | 6 |
| | ወቅታዊ ርእስ | የክርስቲያን ሥነ ምግባር | 6 |
| ፪ኛ ሩብ | ብ.ኪ. | መክብብና መሕልየ መሓልይ | 6 ንግግሮች |
| | አ.ኪ. | ራእይ | 12 |
| | ወቅታዊ ርእስ | ቤተ ክርስቲያንና የወንጌል አገልግሎት | 6 |
| ፫ኛ ሩብ | ብ.ኪ. | ከአሞጽ - ሶፎንያስ | 12 ንግግሮች |
| | አ.ኪ. | የሉቃስ ወንጌል | 6 |
| | ወቅታዊ ርእስ | ወደ ክርስቶስ መመለስ | 6 |
| ፬ኛ ሩብ | ብ.ኪ. | ዘሌዋውያን፥ ዘኍልቍ | 6 ንግግሮች |
| | አ.ኪ. | ገላትያ | 6 |
| | | 1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ | 6 |
| | ወቅታዊ ርእስ | መንፈስ ቅዱስ | 6 |

| ዕቅድ - መ | | | |
|---|---|---|---|
| ፩ኛ ሩብ | ብ.ኪ. | ዕዝራ፥ ነህምያ ፥ አስቴር | 6 ንግግሮች |
| | | ኢዮብ | 6 |
| | አ.ኪ. | ዮሐንስ 13-21 | 6 |
| | ወቅታዊ ርእስ | የክርስቲያን ሕይወትና አገልግሎት | 6 |
| ፪ኛ ሩብ | ብ.ኪ. | ኢሳይያስ 40-66 | 6 ንግግሮች |
| | አ.ኪ. | ዕብራውያን ፥ ያዕቆብ | 12 |
| | ወቅታዊ ርእሶች | ባዕድ አምልኮዎችና ሌሎች ሃይማኖቶች | 6 |
| ፫ኛ ሩብ | ብ.ኪ. | ዳንኤል | 6 ንግግሮች |
| | | ከሐጌ - ሚልክያስ | 6 |
| | አ.ኪ. | የማቴዎስ፥ የማርቆስ፥ የሉቃስ ወንጌል | 6 |
| | ወቅታዊ ርእስ | ሰማይና ሲኦል (ገሃነም) | 6 |
| ፬ኛ ሩብ | ብ.ኪ. | ዘዳግም | 6 ንግግሮች |
| | አ.ኪ. | ፊልጵስዩስ ፥ ጢሞቴዎስ ፥ ቲቶ | 12 |
| | ወቅታዊ ርእስ | የክርስቶስ ማንነትና ሥራው | 6 |

ከዚህ መርሐ ግብር የሚገኘው ጥቅም በእነዚህ ስብሰባዎች ላይ የሚሰጡት ትምህርቶች በዘፈቀደ የቀረቡ ሳይሆን ሁሉንም ያጠቃለለ ዕቅድና ዐላማ ያላቸው መሆናቸው ነው::

ግልጽ ለመሆን፥ በያንዳንዱ የስብሰባ ፕሮግራም ላይ ይሆናል ተብሎ የሚገመተው የማስተማሪያ ጊዜ ሠላሳ ደቂቃ ብቻ ነው:: በአንዳንድ ሁኔታ ይህ ጊዜ ሊቀነስ ሲችል በሌላ ሁኔታ ደግሞ ሊጨምር ይችላል፤ ያም ሆኖ መርሐ ግብሩን እንደ ዕቅድ ማዕቀፍ አድርገን ልንጠቀምበት እንችላለን::

**የተመጣጠነ ምግብ**

መርሐ ግብሩ ሦስት ማስተማርያዎችን፥ ብሉይ ኪዳንን፥ አዲስ ኪዳንንና ወቅታዊ ርእሶችን ያካተተ ነው:: ዓመቱ በአራት ሩቦች የተከፋፈለ እንደመሆኑ መጠን እያንዳንዱ የማስተማርያ ዝግጅት በአራት የተከፋፈለ ነው፤ ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን በያንዳንዱ ሩብ ከብሉይ ኪዳን፥ ከአዲስ ኪዳንና ከወቅታዊ ርእስ ጉዳዮች ትምህርት ታገኛለች:: የተቀናጀውን የአራቱን ሩብ ይዘት ብንመለከት ቤተ ክርስቲያን ለዓመታት በብዙ ቅዱሳት መጻሕፍትና በወቅታዊ ርእሶች ትምህርት ስታገኝ እንደነበረ እንረዳለን::

በገጽ 112-113 ላይ የሰፈረው የአንድ ዓመት አራት ዕቅዶች እያንዳንዳቸው የተለያዩ ናቸው:: ምንም እንኳ አንድ ዐይነት አካሄድ ቢከተሉም ቅዱሳት መጻሕፍትን፥ ወቅታዊ ርእስ ጉዳዮችን በተመለከተ ሁሉም ሚዛናዊ ቢሆኑም መለያየት ይታይባቸዋል:: ለአራት ዓመታት በተከታታይነት ብንጠቀምባቸው የቅዱሳት መጻሕፍትንና የልዩ ልዩ አስተምህሮ ዘርፎችን ከአተገባበራቸው ጋር መሸፈን እንችላለን::

መርሐ ግብሩን በምናስተዋውቅበት ጊዜ ስለ አራቱ ዓመታት ጠቅላላ ፕሮግራም አለማሰባችን የተሻለ ነው:: የአንድ ዓመቱን ብቻ በዝርዝር እናቅድና (ለምሳሌ:- ዕቅድ - ሀ -) የቤተ ክርስቲያን ምላሽ ምን እንደ ሆነ እንጠብቃለን:: ብዙ ሰዎች ውጥረት ውስጥ በማስገባት ነጻነት ያሳጡናል ብለው ስለሚሰጉ የረጅም ጊዜ መርሐ ግብር ማውጣቱን አይወዱትም:: ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ የሆነ የዓመቱን መርሐ ግብር በማውጣቷ ረገድ ደስ የሚሰኙ ሲሆኑ በአንጻሩ በምን ምክንያት ጥርጣሬ እንደሚገባቸው መገንዘብ ይቻላል:: ብዙ ዝርዝር ጉዳዮችን አስቀድመን ብንሰጣቸው አብዛኛዎቹ ነገሮች ሊደበላለቁ ይችላሉ፤ ነገር ግን ቢያንስ የሚመጡትን ሳምንታት ወይም ወራት መርሐ ግብሮች በተከታታይ ልናሳውቃቸው ይገባል:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቀጥለው ለሚቀርቡት ንግግሮች ዝግጅት እንዲያግዟቸው ተያያዥነት ያላቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በቤታቸው ውስጥ እንዲያነቡ ማበረታታት አለብን::

በተሞክሮ እንደታየው ከሆነ የአንድ ዓመቱ መርሐ ግብር ደጎና ሊጓዝ ይችላል፥ ወዲያውም የሚቀጥለውን ዓመት (ዕቅድ - ለ - ) መርሐ ግብር አናዘጋጃለን፤ ይህ በደኅና ከዘለቀ የሚቀጥለውን ዓመት መርሐ ግብር (ዕቅድ- ሐ -) ማዘጋጀታችንን እንቀጥላለን:: የአራት ዓመቱን መርሐ ግብር ከፈጸምን በኋላ የመጀመሪያውን መርሐ ግብር እንደ ብለን መጀመር ስለሚኖርብን ይህን የመሰለ ዝግጅት ሳልተወሰነ ጊዜ መቀጠል ይኖርበታል:: እንዲህ ስንል ደግሞ ቀደም ብለን በአራት ዓመት ውስጥ በተጠቀምንባቸው ንግግሮች ዳግም እንጠቀም ማለትም አይደለም፤ ነገር ግን አጠቃላይ የሆነ አካሄድ ወይም ማዕቀፍ መከተል ይኖርብናል:: ስለዚህ በዚያ ማዕቀፍ ውስጥ ሆነን የቅዱሳት መጻሕፍትንና ወቅታዊ ርእሶችን እንዴት እንደምናጠናና እንዴት እንደምናዘጋጅ አዲስ ዘዴዎችን መቀየስ ይኖርብናል::

ይህም ወደ ተግባራዊ ዝርዝር ጉዳዮች ያመጣናል:: በአንድ ዓመት አጠቃላይ መርሐ ግብር ማዕቀፍ ውስጥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችንን የስብከት ዝግጅቶችን እንዴት አድርገን ማቀድ እንችላለን?

## ዝርዝር ጉዳዮችን ማከናወን

ዕቅዳችንን ቀደም አድርገን ብንጀምር ሥራችን የተቃና ይሆናል፤ (የስድስት ወራት ቢሆን ይመረጣል)፤ የአንዱን ሩብ ብቻ እናዘጋጃለን:: ለዚህ ጉዳይ የተመረጡት ተናጋሪዎች የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኒቱን አባላትና ከውጪ የሚጋበዙትን ተሰጥኦ ያላቸውን ሰባኪዎች ያካትታል:: መርሐ ግብሩ በአጥቢያው ውስጥ ያለውን ተሰጥዖ ለማሳደግ ዕድል ይሰጣል:: የአጥቢያ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ችሎታ በተግባር ላይ እንዲያውሉ እንፈልጋለን፤ እናም ችሎታቸውን በተግባር መግለጽ የሚችሉባቸውን ተስማሚ ርእሰ ጉዳዮችንና ሁኔታዎችን እናመቻችላቸዋለን::

አብዛኞዎቹ ሰባኪዎች የምንጠቅስላቸውን መጽሐፍ ወይም ርእሰ ጉዳይ ሊጠቀሙበት ዝግጁዎች ናቸው:: ለዝግጅት የስድስት ወራት ጊዜ ስንሰጣቸው የማያውቁት ርእሰ ጉዳይ ላይ ለመዘጋጀት ጊዜ ይኖራቸዋል:: የቤተ ክርስቲያናችን ወጣት ሠልጣኝ ሰባኪዎች ለሚያካሂዱት ዝግጅት አመራርና እገዛ ይፈልጋሉ:: ሌሎች በሳል የሆኑ ሰባኪዎች ግን ራሳቸውን ችለው ዝግጅታቸውን እንዲያደርጉ ነጻነት መስጠት ነው::

ለምሳሌ አንድ ሰባኪ ከቅዱሳት መጻሕፍት ባንዱ ላይ ስብከት አዘጋጅቶ ንግግሩን ቀጥተኛ በሆነ ማብራሪያና አተገባበር ዘይቤ ሲያቀርብ ሌላው ደግሞ ከመጻሕፍት እያጣቀሰ መናገርን ይመርጣል:: እንዲሁም አንዱ ክፍሎችን ወይም ጥቅሶችን የሚመርጥ ሲሆን ሌላው ደግሞ ከመጽሐፉ ውስጥ በሚያገኛቸው ገጸ ባሕርያት ወይም ርእሶች ላይ መናገርን ይፈልጋል:: የተለያዩ የአጠቃቀም

ዘዴዎች በተለያዩ መንገዶች የመጠቀም ብቃትን ይሰጣሉ:: ከአራት ዓመት በኋላ ወደ ተጠቀምንበት መጽሐፍ ስንመለስ አሁን ከበፊቱ በተለየ መንገድ መጠቀም እንዳለብን ልናረጋግጥ እንችላለን::

የየሩብ ክፍለ ጊዜ ስብሰባን በሚመለከት የምናዘጋጀው ዘገባ እንደየሁኔታው የሚመቻች ሊሆን ይገባል:: ደግሞም በመርሐ ግብሩ ላይ የተመዘገበው ጊዜ እንደ መመሪያ እንዲጥቅም የታቀደ ስለ ሆነ አካባቢውን በሚጠቅም ሁኔታ መጠኑ ሊያንስ ወይም ሊጨምር ይችላል:: አስቸኳይ የሆነና አካባቢውን የሚመለከት ርእሰ ጉዳይ ከተገኘ የተጀመረውን መርሐ ግብር ማቋረጥ ወይም እንደሁኔታው አስማምቶ መጠቀም ይቻላል::

### የአዘገጃጀት ምሳሌዎች

በገጽ 118 - 119 ላይ የሚገኙት ምሳሌዎች በዕቅድ - ሀ - ላይ ያሉት አንደኛና ሁለተኛ ሩብ መርሐ ግብሮች እንዴት እንደሚዘጋጁ ያሳያሉ:: እንደ ስብሰባዎቹ ዐይነትና ስልት ለስብሰባ 1 እና ለስብሰባ 2 የሚመደቡ ርእሰ ጉዳዮች ይለያያሉ:: አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መጻሕፍት በቤተ ክርስቲያን ለሚደረግ ስብከት አመቺ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ለቡድን ውይይት ሊጠቅሙ ይችላሉ:: የአዘገጃጀቱ ምሳሌዎች እንደሚያስረዱት ስብሰባ 2 ሳምንታዊውን መደበኛውን የእሑድ ፕሮግራም የሚመለከት ነው፤ ስለዚህም የመጀመሪያው ሩብ መርሐ ግብር÷ ከመዝሙራት ተመርጠው በገቡ አያሌ ነጥቦች ምክንያት ሁኔታው ተዛንፏል:: ስብሰባ 2 ግን በቤት ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድንን የሚወክል ቢሆን ኖሮ ተከታታዩን ሐሳብ በማቋረጥ ፈንታ በተከታታይ መቀጠል ይቻል ነበር:: ይህ ከሆነ «ቤትና ኅብረተሰብ» በሚል ርእስ ላይ የተዘጋጁት ንግግሮች ለስብሰባ 2 ሊመደቡ ሲችሉ÷ ስድስተኛው በመዝሙራት ላይ ለስብሰባ 1÷ ወይም አመቺ ለሆነው ስብሰባ ሊመደብ ይችላል::

የሩቡን ጊዜ ዝግጅቶች ለማከናወን ሚዛናዊ ለመሆን መሞከር አለብን:: በተለይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስላልሆነ መጽሐፍ በምንናገርበት ጊዜ ተከታታይነትና ተያያዥነት ሊኖረን ይገባል:: በአንጻሩም በተለያዩ መንገዶች መጠቀም አለብን:: ዝርዝር ሐሳቦችን ለማዘጋጀት የሚያቅደው ሰው በተለያዩ መጻሕፍት ላይ ዝግጅቱን ያለ ችግር ለማከናወን እንዲችል ተግባራዊ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ሊኖረው ይገባል::

ምንም እንኳን አንድ ተናጋሪ በመላው መጽሐፍ ላይ እንዲናገር ብንፈልግም ስለ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ሲባል ሌላ ዘዴ ልንሻ እንችላለን:: ለምሳሌ መጽሐፈ መሳፍንትን በተመለከተ ተናጋሪው አንድ ጊዜ ለመጽሐፉ የሚስማማ መግቢያ ወይም ቅኝት ከሰጠ በኋላ ሌሎች ተናጋሪዎች በመቀጠል በተገለጹ አራት መሳፍንት ላይ ንግግር ሊያደርጉ ይችላሉ:: ግን ይህን የመሰለ አካሄድ በሌሎች

መጻሕፍት ላይ አያገለግልም፤ እንዳይሆንም ይመከራል:: ለምሳሌ :- የጥበብ መጻሕፍትን በተመለከተ በመጽሐፈ ምሳሌ ላይ የሚደረገው ንግግር በተለያዩ ተናጋሪዎች፥ በተለያዩ ዘይቤዎች ሊቀርብ ይችላል:: መጽሐፈ መክብብ ግን ሙሉ በሙሉ በአንድ ተናጋሪ መቅረብ ይኖርበታል:: ከማቴዎስ ወንጌል ውስጥ የተመረጡ ክፍሎችን የተለያዩ ተናጋሪዎች እንዲያቀርቧቸው እንፈቅድ ይሆናል፤ የራእይን መጽሐፍ ግን በዚህ አያያዝ እንዲቀርብ ማድረግ አንችልም::

በመርሐ ግብሩ ውስጥ ስለተዘረዘሩ ቅዱሳት መጻሕፍት በመጻሕፍቱ ሁሉ ላይ ንግግር እናቀርባለን ማለት አይደለም:: የኢያሱ፥ የመሳፍንትና የሩት መጻሕፍት ለመጀመሪያው ሩብ ቢመዘገቡም የኢያሱ መጽሐፍ ገና ያልተነካ (ለሌላ ጊዜ የሚቆይ) መሆኑንና በመሳፍንት ላይ የሚደረገው ንግግር በተወሰኑና በተመረጡ ገጸ ባሕርያት ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል::

በሐዋርያት ሥራ ላይ የሚዘጋጁ ስድስት ንግግሮች መጽሐፉን አጠቃሎ ለመጨረስ በቂ ባይሆኑ የንግግሮቹን ቁጥር ብዛት መጨመር እንችላለን:: ይህንንም በሌላ መጽሐፍ ላይ ከሚደረግ ንግግር ላይ በመቀነስ ምናልባትም ከተመደቡ ክፍለ ጊዜያት በሁለቱ በመጠቀም ማድረግ ይቻላል:: ወደ ፊት «ገና የሚወሰን» የሚለውን ስንመለከት በመርሐ ግብር - ሐ - ውስጥ ስድስት ንግግሮች እንደ ተመደቡ እናስተውላለን:: እነዚህም በሐዋርያት ሥራ ላይ የበለጠ ሰፋ አድርገን ለመነጋገር ጊዜ ይሰጡናል:: (በሌላ ስፍራም በመርሐ ግብሩ ውስጥ ለማቴዎስ፥ ለማርቆስና ለሉቃስ ለያንዳንዳቸው ስድስት ንግግሮችን ብናቅድና በቂ ባይሆኑ በዕቅድ - መ - ውስጥ ባለው ጊዜ መጠቀም እንችላለን)::

ለሥራ ልምምዱ ምሳሌ ወደ ሁለተኛው ሩብ ዕቅድ - ሀ - ስንሄድ የመጽሐፈ ምሳሌ አጠቃቀም በሌላ መጽሐፍ መጠቀም ምን እንደ ሆነ ያሳየናል:: በመጽሐፉ ውስጥ ባሉ ካንዱ ምዕራፍ በሌላው፥ በውስጡ ባሉም ጥቅሶች በዝርዝር ማብራሪያ በመጠቀም ፈንታ በመጽሐፉ ውስጥ ተበታትነው ባሉ ርእሰ ጉዳዮች ላይ እንነጋገራለን በእነዚህ ርእሶች ላይ እንዲናገሩ የተወሰኑ ተናጋሪዎችን ብንጋብዝ የተመደቡት ምዕራፎች የሚሠሩባቸውን የተለዩ ርእሰ ጉዳዮችን ይሰጧቸዋል:: ይህም ዝግጅቱ የሚጠይቀውን ጊዜ ያቃልላል:: እዚህ ላይ ንግግሩ ተከታታይ መሆን የለበትም:: ሌላውን መርሐ ግብር ማዘጋጀት የምንችልበትን ሁኔታ በሚወስን መልኩ በነጠላ ወይም በእጥፍ ሊሰጡ ይችላሉ::

በአጥቢያ የሚፈለገው ነገር ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያን፥ ከዓመት ወደ ዓመት በዚያው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይለያያል:: በልምምድ ምሳሌው ውስጥ እንደተገለጸው አንድ ቤተ ክርስቲያን የሮሜን መልእክት በ0ሥራ ሁለት ንግግሮች ሊያጠቃልል ይችላል:: ሌላው ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በሌላ አኳኋን ይፈጽመዋል:: የሥራ ልምምዱ መንገድ ስምንቱ የመጀመሪያ ምዕራፎች በስብሰባ 2 ውስጥ እንዴት ሊገለጹ እንደሚችሉ ያመለክታል:: ሁለተኛዎቹ ስምንት ምዕራፎች ደግሞ በስብሰባ 1 ላይ ሐሳባቸውን ይቀሰቅሳል:: ቤተ ክርስቲያን ከተቀመጠው የንግግር ቁጥር በበለጠ በስፋት

| ዕቅድ - ሀ - የመጀመሪያ ሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|
| ስብሰባ አንድ | | | ስብሰባ ሁለት |
| ወር | ቀን | ርእስ | ርእስ |
| መስከረም | 3 | እውነተኛ አምልኮ (መዝ. 50) | የእግዚአብሔር ምድር (መዝ. 104) |
| » » | 10 | የማይለወጥ አምላክ (መዝ. 102) | ክርስቲያንና ቤተ ሰብ |
| » » | 17 | የይቅርታ ደስታ (መዝ. 32) | ክርስትያንና ኅብረተ ሰብ |
| » » | 24 | (የሚወሰን) | ክርስቲያንና መንግሥት |
| » » | 30 | መሳፍንት እነማን ነበሩ? (የመሳፍንት መግቢያ/ ቅኝት) | በሕይወት በሚገባ መጠቀም (መዝ. 90) |
| ጥቅምት | 7 | ዲቦራ (መሳፍንት 4-5) | ክፋዎች ለምን ይበለጽጋሉ? (መዝ. 77) |
| ጥቅምት | 14 | ጌዴዎን (መሳፍንት 6-8) | ጨቅላዋ ቤተ ክርስቲያን (ሐዋ. 1-7) |
| ጥቅምት | 21 | ዮፍታሔ (መሳፍንት 10-12) | ታዳጊዋ ቤተ ክርስቲያን (ሐዋ. 8-12) |
| ጥቅምት | 28 | ሶምሶን (መሳፍንት 13-16) | ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን (ሐዋ. 13-15) |
| ኅዳር | 7 | ሩትና ቦዔዝ (ሩት. 1-4) | (ገና የሚወሰን) |
| ኅዳር | 14 | ክርስቲያንና ሥራ | ጳውሎስ ወደ አውሮፓ መሄዱ (ሐዋ. 16-18) |
| ኅዳር | 21 | ክርስቲያንና ትርፍ ጊዜ | ቤተ ክርስቲያኖችን ማጠናከር (ሐዋ. 19-20) |
| ኅዳር | 28 | ክርስቲያንና ሥቃይ | ሽንፈት ወደ ድል ሲለወጥ (ሐዋ. 21-28) |

| ዕቅድ - ሀ - ሁለተኛ ሩብ | | | |
|---|---|---|---|
| ስብሰባ 1 | | | ስብሰባ 2 |
| ወር | ቀን | ርእስ | ርእስ |
| ታኅሣስ | 4 | ቤተ ክርስቲያ ምን ምን እንደ ሆነችና ምን እንዳልሆነች | ድነት ለምን አስፈለገ? (ሮሜ. 1) |
| ታኅሣስ | 11 | ስጦታዎች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን | ሃይማኖት አታላይ ሊሆን ይችላል (ሮሜ 2) |
| ታኅሣስ | 18 | ኅብረት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን | ኀጢአተኞች ጻድቃን ይሆናሉ (ሮሜ 3) |
| ታኅሣስ | 25 | ወንጌልን ለወጣቶች የማሠራጨት ስልት | በጸጋ፥ በእምነት አማካይነት (ሮሜ 4-5) |
| ጥር | 2 | የእግዚአብሔርን ጥበብ መማር (ከምሳሌ 1-9) | (ገና የሚወሰን) |
| ጥር | 9 | ራስን ሥርዓት በማስያዝ ማሳደግ (ከምሳሌ 1-9) | ከኀጢአት ነጻ መሆን (ሮሜ 6) |
| ጥር | 16 | ችግር ፈጣሪ አትሁን (ምሳሌ 1-9) | አሮጌውና አዲሱ ሕይወት (ሮሜ 7-8) |
| ጥር | 23 | (ገና የሚወሰን) | የክርስቲያን መታመን (ሮሜ 8) |
| ጥር | 30 | እስራኤል ወደ ስህተት እንዴት እንዳመራ (ሮሜ 9፥10) | በወንጌል ያልተደረሰው ዓለም ተግዳሮት |
| የካቲት | 6 | ታላቁ የእግዚአብሔር ቤተሰብ (ሮሜ 11) | በዓለም የአክራሪ ሃይማኖት አስቸጋሪነት |
| የካቲት | 23 | ክርስቲያኖች በኅብረተሰቡ ወስጥ (ሮሜ 12-13) | ስለ ቍጣ የጥበብ ቃል (ምሳ. 10-17) |
| የካቲት | 20 | መብትና ጥቅም (ሮሜ 14-15) | ስለ ገንዘብ የጥበብ ቃል (ምሳ. 18-24) |
| የካቲት | 27 | ሁልጊዜ አስቀድሞ ማሰብ (ሮሜ 15-16) | ስለ ምኞት ጥበበዊ ቃል (ምሳ. 25-31) |

መጽሐፉን ለማጥናት ብትፈልግ የጥናቱን ጊዜ ልታራዝም ወይም የሚጠኑትን ምዕራፎች ብዛት ልትቀንስ ትችላለች።

በመርሐ ግብሩ ውስጥ የተዘረዘሩት አስተምህሮታዊና ተግባራዊ ርእሰ ጉዳዮች የተለያዩ ክፍሎችን የሚወክሉ ናቸው። ስለሆነም ሌሎችም ትዝ የሚሉን ነጥቦች ካሉ ከርእሶቹ በአንዱ ውስጥ ሊጠቃለሉ ይችላሉ። በሁለተኛው ሩብ የሥራ ልምምድ ምሳሌ ውስጥ ቤተ ክርስቲያንና ሐዋርያዊ ተልእኮ የሚለው ርእስ የተለየ የቤተ ክርስቲያን ዕድገትንና ወንጌል ስርጭትን ይመለከታል። ሆኖም በዚሁ ርእስ ውስጥ ሰፋ ያለ አምልኮ፥ ጸሎትና አመራር ያሉ ነጥቦች በዚህ ርእስ ሥር ሊታከሉ ይችላሉ። በሌላ መንገድ በክርስቲያናዊ ሕይወትና አገልግሎት ሥርም ሊጠቃለሉ ይችላሉ። ይህ ክፍል በጣም ሰፊ ስለ ሆነ በሌላ ስፍራ ያልተሸፈኑትን ርእሶች ሁሉ ማካተት ይችላል።

የማስተማሩን ዝግጅት በፈለግነው ሁኔታ ብናቅደውም ምንጊዜም ማሰብ ያለብን ፣ የመርሐ ግብሩ ዓላማ የያንዳንዱን መጸሐፍ ምዕራፍ ማዳረስና መፈጸም አለመሆኑን ነው። እያንዳንዱን ርእስ መሸፈን ማለትም አይደለም። በዚህ ፈንታ የተፈለገው ቁምነገር ተመጣጣኝ ትምህርትን መመገብ ነው። በዚህም በያመቱ ተከታታይ በሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍት በክርስቲያን አስተምህሮና በተግባራዊ የትምህርት ዐይነቶች አማካይነት ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ቤተ ክርስቲያንን መመገብ እንችላለን።